# ውግዘት የስሜት መግለጫ አይደለም!

የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Reserved

መጀመሪያ ኅትመ መጋቢት 2006 ዓ.ም.።
ሲያትል ዋሽንግተን አሜሪካ።

Copyright 2014 Amare Afelae Bishaw
First Edition March, 2014
Printed in
U.S.A

Published by Gugsa Magazine
P.O.BOX 492
SEATTLE, WA 98111
U.S.A.

የጸሐፊው መልዕክት ሣጥን ቁጥር
P.O.BOX 492
SEATTLE, WA 98111
U.S.A.

ከአማረ አፈለ ብሻው፤
AMARE AFELAE BISHAW

## ማውጫ

### ክፍል አንድ


ምዕራፍ 1 ማውጫ፤መታሰቢያና ምስጋና ገጽ 1-5
ምዕራፍ 2 ፊር አስጨባጭ ገጽ 6-13
ምዕራፍ 3 ወያኔ ሲጀመር ጀምሮ ፀረ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ገጽ 14-26
ምዕራፍ 4 ስ/ሲ/ ሊጠቃ የቻለበት ምክንያት በአጭሩ ሲዳሰስ ገጽ 27-32


### ክፍል ሁለት


ምዕራፍ 1 ሐዲስ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሣኤ ሆኑ እንዲታሰሩ ገጽ 33-39
ምዕራፍ 2 አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ በተለያዩ ቦታዎች ተባረሩ ገጽ 40-45
ምዕራፍ 3 መላከ ጸሐይ ቀሲስ ዘማሪ እንዳልካቸው ከሥራ ተባረሩ ገጽ 56-48
ምዕራፍ 4 ሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ ባወቅ ሆኑ እንዲጠሉ ገጽ 49-50
ምዕራፍ 5 መምሕር ተከስተ ጫኔ ያሳሉትን አሉ ተብለው ተከሰሱ፤ ገጽ 51-53
ምዕራፍ 6 አባ ቃለ ጽድቅ ሙሉጌታ መጋጨት የፈጠረው ችግር ገጽ 54-58


### ክፍል ሦስት


ምዕራፍ 1 ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ተሳደዱ ገጽ 59-65
ምዕራፍ 2 ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ሆኑ እንዲጠሉ ገጽ 66-69
ምዕራፍ 3 ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የገጠማቸው ፈተና፤ ገጽ 70-75


### ክፍል አራት


ምዕራፍ 1 ቅዱስነታቸውን ወያኔም ከዚህ በላይ አሳሳደዳቸው ገጽ76-92
ምዕራፍ 2 ሕ/ቀ ሲኖዶስ እንዲጠነክር ጳጳሳቱና ካህናቱ አይፈልጉም! ገጽ 93-101
ምዕራፍ 3 ምዕመኑ ሰሚ በማጣቱ መሰቃየቱ! ገጽ102-110
ምዕራፍ 4 ብፁዑ አቡነ መልከጸዲቅን ስለምናከብር እንዲከበሩ ጣርን! ገጽ 111-114


### ክፍል አምስት


ምዕራፍ 1 ውግዘትና ልዩነት በዓም ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ገጽ 115-124
ምዕራፍ 2 የኢ.ኦ.ተ.ቤተ ክ. ምዕመናን በካህናት መሰቃየት ገጽ 125-129
ምዕራፍ 3 የኢ.ኦ.ቤተ ክ.ጳጳሳት መሰደድና መወጋገዝ ገጽ 130-134
ምዕራፍ 4 ውግዘት የስሜት መግለጫ አይደለም ገጽ 135-147
ምዕራፍ 5 ጠቅላላ ሠነድ ገጽ 148-150




# ክፍል አንድ

# ምዕራፍ አንድ

## መታሰቢያ

ዕብ፲፫፡7"ዋናዎቻችሁን አስቡ"ባለው መሠረት ጥሩ የሰሩ ዜጎች ሊታሰቡ ይገባል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያን ወያኔ በመጀመሪያ ከስልጣን አውርዶ ከአገር እንዲወጡ አስገደዳቸው። ኬንያ ከገቡ በኋላ ወደ ሌላ አገር እንዳይወጡ ጥሯል። ይህን ያደረገው በሌሊት አፍኖ ኢትዮጵያ ለመውሰድ እቅድ ነበረው። በስደት የሚገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ ጥር 28 ቀን 1999 ዓም መግለጫ ዋቢ ነው።

<u>በኢትዮጵያ በሰሜን አሜሪካና በመላው አውሮፓ</u> ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤ በተባለው መጣጥፍ ገጽ 2 "ኬንያ በነበሩበት ጊዜ ያሉበት ቦታ ተጠንቶ አደጋ እንዲጣልባቸው ብዙ ሙከራ ተደርጎ እንደነበር የታወቀ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃ ስላልተለያቸው ይኸውና እስካሁን ድረስ በሕይዎት ቆይተው ታላቅ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ"ሲል መጣጥፉ ያብራራል። በዚህ ወቅት በእግዚአብሔር ፈቃድ የሲያትል የጎንደር ማህበር ጥረት ወደ አሜሪካ እንዲገቡ ተደረገ።

ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቅድሚያ መምህራችን ይመለሱ ብለው ኋላም የቤተ ክርስቲያናችን ቃለ አዋዲው ይከበር ብለው ተነሱ፤ዛሬም አሉ። በዚህ ወቅት ከአባቶች ጋር ለማስማማት አዛውንቶች ጥረት አደረጉ። ከነዚህ መካከል ግንባር ቀደሙ አቶ ፍቅሩ ክፍሌ፤የሚደርስባቸውን ጥላቻ ችላ ብለው ለሰላም ሲጥሩ አይቻቸዋለሁ።

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከ1986-2005 ዓም ተቋም አልነበረውም። ነሐሴ 23 ቀን 2005 ዓም ከብዙ ጥረት በኋላ በሲኖዶሱ ስም ቤት ተገዝቷል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ብር እንዲሰበሰብ ያደረጉ ሁሉ ይህ የመጀመሪያ ቅርስ ላይ መሠረት ጥለዋል።

# ምዕራፍ 2

## ፊር አስጨባጭ!

ሕዝቃኤል 3፤1 "የሰው ልጅ ሆይ፤ያገኘኸውን ብላ!ይህን መጽሐፍ ብላ ሂደህም ለእስራኤል ቤት ተናገር አለኝ"ይላል፤ነቢዩ ሕዝቃኤል አንባብያን ይህን ውግዘት የስሜት መግለጫ አይደለም ያልኩትን መጽሐፍ ስትመለከቱ ብዙዎቻችሁ ከልብ እንደምታዝኑ አውቃለሁ:: ከዚህ በፊት ጉግሣ መጽሔት አዘጋጅ ነበርኩኝ:: ቆይቼም መጻሕፍት ስጽፍ ብዙ ምሁራንን በሚጽፉት መጻሕፍት ሆነ መጣጥፍ ተችቼ ጽፌአለሁ:: አሁን በዚህ መጽሐፍ የምተቸው ጎንደሮችን ነው::

እኔ ወርቁን ጽዮን ደብር፤ግራሪያ ምክትል፤ፋርጣ ወረዳ፤ደብረታቦር አውራጃ፤ጎንደር ክፍለ ሀገር፤እትብቴ የተቀበረ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነኝ:: እኛ የፋርጣ ልጆች ወላጆቻችን ያሳደጉን ሰፈዋን ኢትዮጵያ እንጂ ጠባብነትን አላስተማሩነም:: እኛ በተወለድንበት ወረዳ እቴጌ ጣይቱ ብጡል የቀድሞዋ፤የአሁኑ አቶ አንዱዓለም አራጌና ሌሎች አገርና ሕዝብ ወዳድ አርቆ አሳቢ ኢትዮጵያውያን እትብታቸው ተቀብሮበታል:: ዓያቶቻችን ኢትዮጵያን አስቀድሙ አሉን እንጂ ሰፈርን አስቀድሙ ብለው አላስተማሩነም:: ዛሬ ጎንደሮች በሚበዙበት ጳጳሳትና መነኮሳት ሊቅ ዶ/ር ሲያጠፉ ድክመታቸውን ሳልፈው አልፈልግም:: በዚህ ምክንያት ሰሞት አትቅበሩኝ እውነቱን እጽፋለሁ ከ2003 ዓም ወዲህ ባስገቡኝ አልክ መሠረት መፈክሬ ይች ናት:: ይችን ግጥም አትላንታ የአጤ ቴዎድሮስ መጽሐፍ ምርቃ አንብቤአታለሁ፤ በቋጠሮ ድረገጽም ወጥታለች፤ከዚያም ደግሞ::

አማረ አፈረ ብሻው <u>ደም አይፍሰስ በቃ የሕወሓት ማኒፌስቶ</u> ያብቃ በተባለው መጽሐፌ ገጽ 61
"የእኔ ለኔ የሚል ቫይረስ ከመንደሬ ገብቶ
አልነቀል አለኝ በጥቅም ተጠቅቶ
የሀገሬን ክብር ታሪኬን የማልሸጥ
ለቤትና መሬት ለጥቅም እማርጥ
ሴረኛን አልወድም ትውልድ አሳፋሪ
እምነቴን አልሸጥም ለጥቅም አዳሪ
ሰሞት አትቅበሩኝ ልውደቅ ልበስብስ



አልሆንም ዘረኛ አገር የሚያፈርስ"::

ብዬ ጽፌ ነበር:: ዛሬም መፈክሬ ይህ ነው:: ስለዚህ ትውልድ አገሬን ኢትዮጵያን የጎዳት ነገር ቢኖር እውነትን በሰፈርተኝነት እየተሸፈነ ነው:: እኔ ደግሜ ደጋግሜ የምለው እውነትን በሰፈርተኝነት ልሸፍናት አልችልም:: የወረዳዬ ልጆች በወረዳው ስም አትነግዱ ይህ መልዕክቴና አቅዋሜ ነው::
ለእውነት ለቆመው ለአንዱዓለም አራጌ ሕዱና ንገሩት
የወረዳህ ልጆች ሰፈርተኛ ሆኑ ብላችሁ አስረዱት::

ሌላው የሰነድ እጥረት ያለባቸው ግለሰቦች "ጎንደሮች በተኗት" ይላሉ ይህ ትክክል አይደለም:: ባይሆን ዛሬ በስደት ያለውን ሲኖዶስ የኔ የወረዳ ልጆች ቁጥራቸው 5 የማይሞሉ ሊከፍል እየጣረ ነው ከተባለ ትክክል ነው:: ይህም ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን ይዞ የሚጓዘው የወያኔ ወደገባ ቡድን ነው:: ግን በስደት አገር ያለውን ቤተ ክርስቲያንን ጎንደሮች አልከፈሉም:: ታሪኩ እንዲህ ነው:: ጥር 13 ቀን 1971 ዓም የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ ዘሕወሓት የሾሟቸውን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን በ1974 ዓም አውግዘው ወደ አውሮፓ ኋላም ወደ አሜሪካ መጡና የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ::

ከዚያም ብፁዕ ወጣዮት አቡነ ጳውሎስ ለትምህርት መጥተው ከዚሁ በመቅረታቸው የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ:: ብፁዕ አቡነ ይስሀቅ በሲኖዶሱ ስር ሁነው በካናዳ፤በአሜሪካና በካሪቢያን፤ እየተዘዋወሩ ቤተ ክርስቲያንን ሲያቋቁሙ አላሰራቸው ብለው የነበሩት ከላይ ስማቸውን የጠቀስኳቸው ሁለት ሊቃነ ጳጳሳት ነበሩ:: እነዚህ ሦስቱ የአንድ ክፍለ ሀገር ተወላጆች ሲሆኑ ብፁዕ አቡነ ይስሀቅ እናታቸው አድዋ፤አባታቸው መንዝ ሸዋ ሲሆኑ እትብታቸው የተቀበረው ትግራይ አድዋ ነው:: እንዲያውም ብፁዕ ወጣዮት አቡነ ጳውሎስና ብፁዕ አቡነ ይስሃቅ የስጋ ዝምድና እንዳላቸው ይነገራል:: ይህ በዚህ እንዳለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ነሐሴ 29 ቀን 1980 ዓም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እንደተባሉ በአሜሪካ በሦስት የተከፈለውን ቤተ ክርስቲያን አንድ ለማድረግ በስደት ያሉትን ጳጳሳት ወደ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲመለሱ ሽምጋይ ልከዋል:: ሉዕኩ የመጣው በ1982 ዓም ሲሆን አባላቱ እነዚህ ነበሩ::

1ኛ ብፁዕ አቡነ ጢሞትዮስ
2 ብፁዕ አቡነ ይስሃቅ የአሜሪካ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ
3ኛ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣
4ኛ ሊቅ ዶ/ር ማርቆስ ወልደ ኢየሱስ፣ ሲሆኑ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የዛሬው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ናቸው::

ሽምግልናውን ብፁዕ አፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ ሆኑ ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ አልተቀበሉም:: ብፁዕ አፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ ዘሕወሓት ግንቦት 1983 ዓም በኢትዮጵያ ርቪው መጽሔት ያልገቡበትን ምክንያት ጽፈዋል:: ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓም ወያኔ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ሁለቱ ጳጳሳት ወደ አዲስ አበባ ገቡ:: ከዚያም የወያኔው ቡድን ሴረኛና ስልጣን የፈለጉትን ጳጳሳት አደራጅቶ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ "ታመዋል"አስብሎ ከስልጣን አወረዳቸው:: ብፁዕ አቡነ ይስሀቅ ኑሮአቸው አሜሪካ ስለነበር ወዲያው ተመለሱ:: ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስና ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ፣ አሜሪካ መጡ:: ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ከአውሮፓ ወደ አሜሪካ መስከረም 1986 ዓም መጥተው ከሌሎች ዘመናዊ ምሁራን ጋር ሁነው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አቋቋሙ:: ይህ በዚህ እንዳለ ዘመናዊ ምሁራን ብፁዕ አቡነ ይስሃቅን ይዘው ለብቻ ሄዱ:: በወቅቱ ሲኖዶስ መቋቋሙን ደግፈው የነበሩ ምሁራንና አንዳንድ ካህናት ሆኑ ሌሎች "ጎንደሮች በስደት ያቸውን ቤተ ክርስቲያን ከፈሏት" ብለው አወሩ:: ይህ ትክክል አይደለም፣ሊታረም ይገባዋል::

እኛ ስናድግ የተማርነው ነገር ቢኖር ትልቅን አክብሩ ተብለን ነው:: ነገር ግን ትልቅ ሲሳሳት ዝም ብሎ ማለት ጥሩ አይመስለኝም:: እኔ የማስበው ለቤተ ክርስቲያን ነው:: 2ቆሮንቶስ 11 "እኔን እለት እለት የሚያሳስበኝ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ነው"ይላል:: እኔን እናት ቤተ ክርስቲያን በ40 ቀኔ ክርስትና አንስታ ልጅ ያደረገችኝ ከፍ ስል ፊደል አስቆጥራ ያሳደገችኝ ናት:: ስለዚህ እኔ የግለሰብ ጠበቃ መሆንን አልፈልግም:: ጠበቃ መሆን የምፈልገው የተቋም ነው:: ተቋም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት:: ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በሴረኞች ስትጠፋ ዝም ማለት አልችልም:: አሁን በብዛት አባቶቻችን የጠሉትን ለማራቅ ሲፈልጉ" ተወግዟል" የሚሉት ቋንቋ ትክክል አይደለም:: ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ውግዘትን ዛሬ ማስፈራሪያ ያደረጉት ግለሰቦች ቁጥራቸው በርክቷል:: የሐዋ ሥራ 10፡39" በተደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን" ይላል:: እኔ ያልሆነና ያልተባለ



ነገር ተባለ ብዬ አልጽፍም:: ከዚህ በፊት በብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ሲኖዶስ ላይ ድክመታቸውን ጠቅሼ ስጽፍ ቆይቻለሁ:: ነገር ግን በእነሱ ላይ አጠንክሬ ስጽፍ የቆየሁት እርሳቸው ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመናገራቸው አይደለም:: ይህ ቅድሚያ እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ::

ሌላው አሁን በቅርቡ እኔን ዝም ለማሰኘት ታስቦ በዲሲ አንድን ጸሐፊ በስም አጥፊነት ከሰው ሃያ ሽ ብር ያስፈረዱበት መሆናቸውን ተደጋግሞ እየተነገረኝ ነው:: የሰው ልጅ አምኖ እንጂ ፈርቶ አይሞትም:: ሁሌም ወያኔ እንዳስፈራራኝ ነው:: በመጀመሪያ አስብ የኢትዮጵያ አካል ነች፣እና ከጋምቤላ እስከ ሁመራ የተባለው መጽሐፌ ከታተመ ወዲህ ደጋግመው አስፈራርተውኛል:: እኔን የሚጠብቀኝ እግዚአብሔር በመሆኑ እስካሁን አለሁ:: እኔን አንድ ነገር አድርጋችሁ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ብትተውልኝ ደስ ይለኛል:: እኔ በሕይዎት እስካለሁ ድረስ ከነዚህ ልለይ አልችልም::እኔ በምቀርባቸው ልጆች አማካኝነት ትክክል እየተሰራ አለመሆኑን ተናግሬአለሁ:: አሁንም ቢሆን የማውቀውን ከመግለጽ አልቆጠብም:: ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን ወንጌላውያን አሳደዋቸው ቢሆን ኑሮ ቀድሜ ጠበቃ በሆንኳቸው ነበር:: ነገር ግን እርሳቸውን ሊያጠቃ የተነሳ የለም:: ይህ ውግዘት የስሜት መግለጫ አይደለም ያልኩትን መጽሐፍ 5 ክፍል እና 23 ምዕራፍ አለው::

ክፍል አንድ መታሰቢያ ምስጋና ከዚያም ፈር አስጨባጭ፣ብሎ ወያኔ ሲጀመር ጀምሮ ፀረ ቤተ ክርስቲያን መሆኑን በሰነድ አስደግፎ ያትታል:: ሕጋውው ቅዱስ ሲኖዶስ ከተቋቋመ ጀምሮ በኢትዮጵያ አንድነትና በቤተ ክርስቲያን ላይ አጠንክሮ መግለጫ ያወጣል፣ሕዝብ መከፋፈሉን ይጠላል:: በዓለም የተበተነውን ሕዝብ ሰባኪ ልኮ ወደ ስደተኛው ሲኖዶስ እንዲገቡ አድርጓል:: በዚህ ምክንያት ቅድሚያ የሲኖዶሱ ጣራና ማገር የሆኑትን ወንጌላውያን እንዲሳደዱ የተደረገው ስለ አንድነት ስለሰበኩ ነው::

ክፍል ሁለት የወያኔ ወዶገባ ቡድን በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ስም ተጠቅሞ ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ ለመበተን ጥረት እያደረገ ነው:: ወያኔ "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ"ብሎ በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ ወዶገባዎችን አስገብቶአል:: ለዚህም ወንጌላውያን እንዲሳደዱ

ተደርጓል። ለወደፊቱም ሊወገዙ እየተደገሰባቸው ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ብፁዕ አቡነ መልኪጼዴቅን የያዙ ቡድኖች ሴራ አልጋለጥ በማለቱ ነው። የወያኔው ወዶገባ ቡድን ብቻ ሳይሆን የጥቅም ሰዎች ሊቀ ጳጳሱን ቀንና ማታ አሳቢ መስለው በመቅረባቸው ነው።

ክፍል ሦስት ጳጳሳቱን ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ጋር እያጋጩ ልዩነት እንዲፈጠር በማድረግ ላይ ስለሆኑ የሚጠሉት ወንጌላውያን ብቻም ሳይሆኑ ጳጳሰትም ናቸው። ከሚገርመው ነገር አንዱ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ ሊቀ ጳጳሱን ሰበካ ጉባኤ ቅስና እንዳይሰጡ ከልክሏል። በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አለ። ያም ሥርዓት ክህነት መስጠት ያለባቸው ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው። በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስር ያሉ ሊቃነ ጳጳሳት ይህን ተግባር እንዳይፈጽሙ ሰበካ ጉባኤው ከልክሏል። ለምን? ለማን ጥቅም?

ክፍል አራት ወያኔ ገና በትረ ሥልጣኑን እንደያዘ ያሳደዳቸው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱን ነው። በዚህ ሰዓት ሌሎች ጳጳሳት ተባባሪ አልነበሩም ማለት አይደለም። ዛሬም ከ22 ዓመታት በኋላ ቀደም ከሌሎች ጳጳሳት ጋር ሁነው ያሳደዷቸው ጳጳሳት ሕገ ቤተ ክርስቲያን ተጣሰ ብለን ተሰደናል የሚሉት አሁን ደግሞ እነዚህ ጳጳሳት ቅዱስነታቸውን ሲያሳስዱአቸው እንመለከታለን። በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስር ባሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በብዙ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምዕመናን እየተሰቃዩ መሆናቸውን በመጠኑ ይገልጻል።

ክፍል አምስት የዓለም ቤተ ክርስቲያን ችግር አፈጣጠርና መወጋገዝ የታሪክ ሰነድ ጠቅሼ ለማስረዳት እሞክራለሁ። ወደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲገባም ድርብርብ ችግሮች መኖራቸውን ይዘረዝራል። ቀደም ሲል ግብጻውያን ጳጳሳት እንደታቦት ተከብረው በመኖራቸው መጻሕፍ ቅዱስን ሳይሆን ካህናቱ በዓላት አክባሪ ሁነው ምዕመኑን ማሰቃየታቸውን ይገልጻል። አሁን በቅርቡ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ጳጳሳት ወደ ስደቱ ከመጡ ወዲህ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሳው ችግር ያነሳል። እነዚህ ጳጳሳት በሥልጣንና በጥቅም ተጣልተው ተወጋገዙ። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በውጭ አገር በሦስት ጎራ ተለያይተናል። ያ አልበቃ ብሎ አሁን ደግሞ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን ይዘው ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ ሊከፍሉ እየጣሩ መሆናቸውን ይገልጻል።



ማቴ 12፥36 "እኔ እላችኋለሁ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ከቃልህ የተነሳ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሳ ትኮነናለህ" የሚለውን ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት አንብቤዋለሁ። ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀሁት ያለ ምንም ማጋነን እውነት የሆነውን ነው። በነገራችን ላይ እኔ ኃጢአተኛ አይደለሁም አላልም። እኔ ኃጢአተኛ መሆኔን ሉቃስ 18፤13" ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፤ነገር ግን አምላክ ሆይ!እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ" እያለ ደረቱን እንደሚደቃው ቀራጭ መሆኔን አውቃለሁ። 1ኛ ዮሐ 1፤8 "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤እውነትንም በእኛ ውስጥ የለም"ይላል። ግን ደግሞ ኃጢአተኛ ነኝ ብዬ ሴረኞች የሚፈጽሙትን ተንኮል ዝም ማለት አልፈልግም።

ይህን መጽሐፍ ስጽፍ መረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ፤ከቅዱስ ቁርዓን፤ ከታሪክ መጻሕፍት፤መጽሔትና መጣጥፍ፤ጋዜጦችና በራሪ ወረቀቶች በድረገጽ የታተሙትን መግለጫዎችና በሰዎች የተነገሩትን ጥያቄ በማቅረብ ያገኘሁትን መረጃ ሰብስብ አድርጌ ጽፌአለሁ። ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጥር ነው። አንድን መጽሐፍ ሆነ መጣጥፍ ጸሐፊው በተጠቀመበት የማዕረግ ስም ጽፌአለሁ። መረጃ የተጠቀምኩባቸው ከ1 እስከ 4 ገጽ በራሪ ወረቀት፤ ከ5 እስከ 64 ገጽ መጣጥፍ፤ከ65 ገጽ በላይ መጽሐፍ ይባላል። ለዚህ መጽሐፍ የተጠቀምኩባቸው ከመጽሐፉ ጥቅስ ስወስድ በተጠቀሱበት ተርታ ከመጽሐፉ መጨረሻ ተመዝግበዋል።

አንድን መጽሐፍ እስከ ጸሐፊው ስም አንዴ ከጠቀስኩት በኋላ ሁለተኛ ስጠቅሰው የጸሐፊውን ስም ሳይሆን የመጽሐፉን ስም ብቻ እጠቅሳለሁ። መጽሐፉን ቅድሚያ ከጻፍኩኝ በኋላ አስምርበታለሁ። መጽሐፉ የታተመበትን ዓመትና የአሳታሚውን ድርጅት ስም አልጠቀስኩም። ከዚህ መጽሐፍ ላይ ያልተለመዱ ቃላት ስታገኙ ትደነግጣላችሁ። ለምሳሌ ለምን"ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ" እንዳልኳቸው ልግለጽ። ሰው በሕይወቱ እያለ የራሱን ምስል ፎቶ በደንጊያ አያስቀርጽም። እርሳቸው ግን በሕይዎት እያሉ ምስላቸውን ሐውልት አስቀርጸው ያቆሙ ናቸው። በዚህ ምክንያት "ብፁዕ ወጣዖት" እያልኩኝ እጽፋለሁ። ብፁዕ ወአፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ ዘሕወሓት እያልኩኝ የምጽፍበት ምክንያት በሴት ፍቅር የወደቁ በመሆናቸው ነው።

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ደረገጽ <u>አባ ማትያስ</u> በ2005 ዓም በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 18 "ሰው በነገረኝ ሳይሆን ራሴ አይቼ የተረዳሁትን ለብቻቸው ነግሬአቸው ለጊዜው ድንጋጤ በተመላበት አንክሮ ከተቀበሉኝ በኋላ ከገቡበት ልማዳቸው ሊላቀቁ ባለመፈለጋቸው በኮሚቴው ፊት በራሳቸው መኖሪያ ቤት ለራሳቸው ለወይዘሪት ሀረግ ወይን በግልጽ ነግሬ ከዲሲ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን እራሴን አገለልኩ"ሲሉ ጽፈዋል። ይህን ለእኔ የነገሩኝ የዛሬ 24 ዓመት ሲሆን በግጥም መልክ በ2002 ዓም ከመጽሐፍ ላይ ጠቅሼው ነበር።

አማረ አፈለ ብሻው <u>በአጸ ባውሎስና በሣማሳት ምክንያት</u> በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሳው እሳት በተባለው መጽሐፍ ገጽ 363
"ምን ያሉ አባት ናቸው እንዲህ የተጎዱ
በአረጋዊት ፍቅር በጣም የነደዱ
ያውም ዝርጋጋው ከመጀመሪያው
ቋያ ማቃጠሉን ቢተውት ምነው
ከጎድጓዳው ቦታ ከድፋው ወርደው
እሣቱን አንድደው መምጣቱን ይተው
ምን ያሉ ሰው ናቸው የሚልፈሰፈሱ
አገኟቸው ቄሱ በለሏን ሲቀምሱ"
የሚል ጽፌ ነበር፤ተመሳሳይ መጣጥፍ ልጥቀስ።

ዐይናለም ግዛው፤<u>አቡነ ማትያስ</u> (አባ ተክለ ማርያም አስራት ማናቸው ?በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 5 "አቡነ ማቴዎስ አመንኩሰው እማሆይ አብርሃም ብለው በሰየሟቸው የዴንማርክ ተወላጅ በማዳም ክርስቲያን ፔደርሰን ፍቅር ተነድፈው ግንኙነታቸው በጥንቃቄ ይይዙ ዘንድ በገዳማቱ አረጋዊ መነኮሳት ቢመከሩ አሻፈረኝ እንዳሉ ይህን ላለማየትና ላለመስማት አንዳንዶቹ አረጋዊ መነኮሴዎች ከኢየሩሳሌም እየሸሹ ቤተ ልሄምን ወደ መሰሉ ቦታዎች ሌሎች ቅዱሳን ሥፍራዎች እየራቁ በመሄድ እስከመቀመጥ እንደደረሱ ለወትሮው በአቡነ ማትያስ ላይ የሚሰነዝሩ ነቀፋዎችን ከእኔ እኩል የሚያውቀው ስለሌለ" ሲሉ ጽፈዋል።

እንባብያን "ብፁዕ ወአፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ" ያልኩበትን ምክንያት ከላይ ጠቅሻለሁ። "ዘሕወሓት" የሚለው እርሳቸውን የመረጣቸው ሕዝበ ክርስቲያኑ ሳይሆኑ ወያኔ ነው። በወቅቱ ሲወጡ የነበሩትን ጹሑፎች ተከታትላችሁ ከሆነ ብፁዕ አፍቅሮተ ሴት አቡነ



ማትያስ ዘሕወሓት ዜግናቸው አሜሪካዊ ናቸው። አንዳንድ ጳጳሳት አስቀድመው እርሳቸው እንደሚመረጡ ስለጠረጠሩ የአስመራጭ ኮሚቴው ሕገ ደንብ "1ኛ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ"ይላል። እርሳቸው ሊመረጡ ሲቀርቡ ጳጳሳቱ ዜግነታቸውን አስመልክቶ ሲጠይቋቸው እንደመለሱ ተናገሩ። በነገራችን ላይ ብጹዕ አፍቅሮተ ሴት ቀደም የደርግ ትልቅ ሰው ነበሩ።

ፍቅረሥላሴ ወግደረስ <u>እኛና አብዮቱ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 207 "ጳጳስ አቡነ ማትያስ ናቸው"ሲሉ ጽፈዋል። የደርግ መንግሥት ጠቅላይ ምኒስትር የነበሩት ሻምበል ፍቅረሥላሴ" ጳጳስ አቡነ ማትያስ ናቸው"ያሉበት ምክንያት እንዲህ ነው። ደርግ ለአብዮቱ ቅርበት የነበራቸውን ሰዎች መርጦ "ለውጥ ሐዋርያ"ብሎ በየክፍለ ሀገራቱ ልኮአቸው ነበር። ከነዚህም አንዱ የዛሬው አፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ ነበሩ። በዚህ ውለታቸው ጵጵስና ስልጣን ተቀበሉና ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። ከዚያም ወደ አሜሪካ መጡ። ሌላው ቀደም ሲል ወያኔ ማለት ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነውን ማለት ነበር!ዛሬ ደግሞ ወያኔ ማለት እንደዱሮው ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪውን ሳይሆን ወያኔ ማለት ከማንኛውም ጎሳና ክፍለ ሀገር የመጡ ለጥቅም የታዘዙትን ማለት ነው። የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ሁሉም በሀሰት መናገር የሚችሉ ሁነዋል።

ለዚህ ሳይሆን ይቀር እንዴ መጽሐፈ ሲራክ 23፤11"የእግዚአብሔርን ስም በሐሰት የሚጠራ ሰው ከመቅሠፍት አይነጻም"የሚለውን ለመፈጸም የፈለጉ ሁሉ በሕዝብና በአካባቢ ስም እየማሉ ይገኛሉ። እንባብያንን ይቅርታ የምጠይቀው ይህ መጽሐፍ የፊደል ግድፈት የአርፍተ ነገር አሰካኩን ድክመት እያቃናችሁ ታነቡት ዘንድ በትህትና አሳስባለሁ። አንድ ሰው ጽፎ ራሱ ሊያርመው አይችልም። ምክንያቱም ጹሑፍና ጨዋታ በፍጹም ሊጠራ አይችልም። ሌላ ሰው ካላየው በቀር። በዚህ መጽሐፍ በማንኛውም ነገር ተጠያቂው እኔ እንጅ ማንም ሊሆን አይችልም።

መልካም ንባብ ይሁንላችሁ
አማረ አፈለ ብሻው፤
መጋቢት 2006 ዓም
መጋቢት 2014

# ምራዕፍ 3

## ወያኔ ሲጀመር ጀምሮ ፀረ ቤተ ክርስቲያን ነው፤

አባቶቻችን "ያዲቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም"ይላሉ። ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ ፀረ ቤተ ክርስቲያን ነው። ይህን ታሪክ በወቅቱ የሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴና የጦር አዛዥ የነበሩት ሊቅ ዶ/ር አረጋዊ በርሔ በመጽሐፋቸው ጽፈውታል። ሌሎች የትግራይ ልጆችም እንደርሳቸው ያሉ ኢትዮጵያውያን ጽፈዋል።

ዶ/ር አረጋዊ በርሄ <u>Political History of the Tigray People,s Liberation Front (1975-1991)</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 246 in Tigray from the wider Ethiopian Church in order to foster Tigraian nationalism along the of the TPLF straegic objective. Suppressed Tigrian natiolism was invoked to challenge the dominant Ethiopian Orthodox Church The initial werda seminars for for the prists were conducted by an eloquent TPLF fighter,Gebre Kidan Desta,a graduate of the theological College at Addis Ababa university.The themes of the semes were to replace the Ethiopian Church authority by TPLF-minded church and the language in the church with Tigrigan and ultimately,to further Tigraian nationalism and identity ሲሉ ጽፈዋል።

ሊቅ አረጋዊ እንዳሉት ወያኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት የተነሳ ድርጅት ነው። ለምሳሌ አቶ መኮንን ዘለለው በአጥኖት የሚገልጹት ወያኔ መምህር ገብረ ኪዳን ደስታን ይዞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ክበር የተሸፈነበትን የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ እየፈቱ የሕወሓት ባንዲራ እንዲለብስ መደረጉን ጽፈዋል። አቶ ገብረ መድህን አርአያ፤ወያኔ የገዳም ንብረት መዝረፉን የዓይን ምስክር መሆናቸውን አስረግጠው ጽፈዋል።



መኮንን ዘለለው <u>ጥላቻና የመከፋፈል አባዜ ይቁም</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 11 "በቅድሚያ ገብረ ኪዳን ደስታ ማነው?መምህር ገብረ ኪዳን ማለት በኢትዮጵያ አንድነት የማያምን ትግራይ ኢትዮጵያ ከሚባል አገር ተነጥላ የራስዋ መንግሥት እንዲኖራት የሚፈልግ ይህ ካልተሳካም አንድ ቋንቋ ከሚናገሩ ከኤርትራ እንድትለጠፍ የሚፈልግ፤የአክሱም ታሪክ የትግራይ ትግርኝ ሕዝብ ታሪክ ብቻ ነው ብሎ የሚያምን ሰው ነው። ይህንን ዓላማውን እውን ለማድረግ ወደ ትሓህት ገብቶ ከስብሃት ነጋ፤አባይ ፀሀይና መለስ ዜናዊ ጋር በማበር ለማንም ታጋይ ተደርጎ የማያውቀውን በበቅሎ እየተንቀሳቀሰ የመንፈሳዊ ትምህርት ትዎሎጂ ምሩቅ በመሆኑ በግእዝ ችሎታውና አካዳሚ ዕውቀቱ ካሉት ቀሳውስት የበለጠ ስለነበር ባለው ችሎታ በቤተ ክርስቲያኖቻችን የነበረውን የኢትዮጵያ ባንዲራ የተሸፈነበትን ክበርና አልባሳት በሙሉ ጠፍቶ በህወሓት ባንዴራ ቀለሞች እንዲተካ በማድረግ"ሲሉ ጽፈዋል። ገዳማቱ እንደተዘረፉ የዓይን ምስክሩ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል።

ገብረ መድህን አርአያ <u>የዘረፉ ውሎ በእንዳማርያም</u> ባሉት በድረገጽ የወጣ በራሪ ገጽ 2 "ሀለቃ ፀጋይ በርሄ በስበሃት ነጋ በታዘዘው መሠረት አስቀድሞ ጥናቱን ጨርሶ ስለነበር የቤተ ክርስቲያኑን አቃቤ ግምጃ ቤት ባህታዊ ማን መሆናቸውን እና የት አካባቢ እንደሚኖሩ አውቋል። ሌሎቻችን ታጣፊ ክላሽኮፕ ስብሃት ነጋ ደግሞ ሽጉጥ ታጥቋል። ለምን እና ወዴት እንደምንሄድ ቀሺ ታደሰ፤ አጽብሃ ኃይለማርያም ሆነ እኔ አናውቅም፡ ኋላም ተጉዘን እንዳማርያም ቤተ ክርስቲያን ገባን። በጥንት በአብርሃ አጽብሃ ዘመን መንግሥት የተሠራ በጣም ሰፊና ብዙ የአትክልት እና ፍራፍሬ እርሻ የሚለማበት ገዳም ነው። መነኮሳት ጉልበት በመስኖ የለማ ሎሚ፤ ሙዝ ብርቱካን፤ትርንጎ፤መንደሪን፤ገዳሙን ከቦታል። መቼም አካባቢው ውብ እና ለመንፈሳዊ ሕይዎት የተመቸ ነው። በእድሜ የበለጸጉ ባህታውያን ቀሳውስት መናንያን እና ዲያቆናት በገዳሙ ዙሪያ መንፈሳዊ ሕይዎታቸውን ይመራሉ።"

"ውስጥ ለውስጥ ብዙ ከሄድን በኋላ ከፊታችን አንድ ዲያቆን አገኘን። ሃለቃ ፀጋይ ዲያቆኑን ለብቻ ነጥሎ አናገረው፤ምን እንደተነጋገሩ እኔ ካለሁበት ብዙም አይሰማም ብቻ ሁለቱ ተያይዘው ከፊት እየመሩ ወደ አንድ ቤት ውስጥ አስገቡን። ቀጥሎም ስብሃት ነጋ እንዲህ አለ፤ ሌሎቻችሁ እዚህ ቆዩ፤እኔ ገ/መድህን እና ሃለቃ ፀጋይ ብቻ የገዳሙን

"ከዚህ በፊት ጀርመን የተባለ አገር በታሪክ አልነበረም። አንድነቱን የመፍጠሩ ሥራ ለዘመናት በሰላም ቢሞከር ከንቱ ቀረ። በመጨረሻ ጀርመን ተዋሂዳ ዛሬ በዓለም የምትድነቅ አንድ ታላቅ ሀገር ለመሆን የበቃችው። ያኔ የፕሩሲያ መሪ የነበረው አቶ ቢስማክ በብረትና በደም ከሚለው መፈክሩ ተነስቶ ከጎረቤቱ መንግሥታት ጋር ባጧጧፈው የጦርነት ኃይልና ባፈሰሰው ደም ነው። ምኒልክ ግን አንድነቷ በተናደው በሁለት መቶ ያህል ዓለም ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው ኢትዮጵያን መልሰው አዋህዷት"ሲሉ ጽፈዋል።

ወያኔ የኢትዮጵያን አንድነት ለመናድ አንዴ ጎሳውን አንዴ ነገሥታቱን እያነሳ ያስድባቸውና ያዋርዳቸዋል። የወያኔን ቅስቀሳ የተቀበሉ አንዳንድ የፕሮቴስታንት አማኞች "የምኒሊክ ሃይማኖት" እያሉ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ያጥላሏታል። ወያኔ ከዚህ በፊት የነበሩት ነገሥታት እንዳቸው በታሪክ እንዲነሱ አይፈልግም። ምክንያቱም አንድነት ለወያኔ በሽታው ነው። ወያኔ የሚወዳቸው እርሱ ያለውን የሚቀበሉ ከሆነ ጠብና ግጭት አያነሳባቸውም። ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ በፀረ ኢትዮጵያ አንድነት ላይ ያተኮረ ነው። ለዚህም በዘር የትግራይን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊለይ ቅድሚያ ማኒፌስቶው እንዲህ ብሎ ጽፎት ነበር።

<u>የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ መግለጫ ማኒፌስቶ</u> የካቲት 1968 ዓም በየካቲት ወር በተባለው መጽሔታቸው "ህ.ዓላማውና ሥራው የትግራይ ሕዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ አማራ ብሔራዊ ጭቆና"ናው ብሎ ሰብኳል። ይህን አስፋፍቶ የትግራይ ሕዝብ በፀረ አማራ ትግል ቀስቅሶ ሲያስነሳ ይቆይና ወዲያው ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው መሠረት በቤተ ክርስቲያንና በገዳማት ላይ የጥፋት ዘመቻውን አስፋፍቶአል። ወያኔ ትግራይ ውስጥ ይህን ሲያደርግ ኑሮ መላ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትንና ንብረት ዘርፏል። የኢትዮጵያን አንድነት በቤተ ክርስቲያን የሚሰበክ በመሆኑ ይህን ሰብከት እንዳይኖር ጥሯል። የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በግፍ እንዲገደሉ ሁነዋል። የቤተ ክርስቲያን ልጆች ወደ ማይፈልጉበት ተገደው ሕደዋል።

የለንደን ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን <u>በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው</u> በሚል ርዕስ ሐምሌ 12 ቀን 2001 ዓም ከጻፈው በራሪ ገጽ 1 "ወደ 7 ሚሊዮን የሚጠጉ ምዕመናን ተስፋ በመቁረጥ ከቤተ ክርስቲያናቸው



የኮበለሉና ለተለያየ ችግር ሰለባ መሆናቸው"ሲሉ ጽፈዋል። የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ምዕመናኑን ብቻ ሳይሆን ጳጳሳቱን ያስደበደበ ነው። ይህን አስመልክቶ የለንደን ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን የዛሬውን አያድርገውና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጠረውን ችግር ተከታትሎ ትክክል አለመሆኑን ትጽፍ ነበር።

<u>ርዕሰ አድባራት ለንደን ቅድስት ድንግል ማርያም ጥቅምት</u> 3 ቀን 2002 ዓም ገጽ 3" በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ የብፁዕዓን አባቶች ማረፊያ የሆነው ቅዱስ ቦታ የወንበዴዎች ዋሻ የቀማኞች መሸሻ ከመሆን እንዲጸዳ አጥብቀን እንጠይቃለን በተለይ ሐምሌ 8 ቀን 2001 ዓም ምሽት ላይ የብፁዓን አባቶች መኖሪያ በር በመደብደብና በመስበር የግድያ ዛቻ ማስፈራራትና እንግልት በማድረስ የውንብድና ተግባር የፈጸሙና ያስፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ስለፈጸሙት ወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ወደፊትም ቅዱስ ሲኖዶሱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መንበረ ፕትርክናውን ከወንጀለኞች እንዲያጻዳ የብፁዓን አባቶችም ሕልውና በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲጠበቅ"ሲል ጽፎ ነበር። ከድብደባ አልፎ በመርዝ መግደላቸውን በድረገጽ የሞቱትን ጳጳሳት የያዘ መጣጥፍ ተለቆ ነበር።

ገብረ ኪዳን <u>ፓትርያርክ ጳውሎስ ያስፈጀቸው ሊቃነ ጳጳሳት</u> በሚል የወጣው ጹሑፍ የወያኔን ገበና ዘክዝኮ አውጥቶታል። ልጥቀስ ገጽ 1" በ2001 ዓም ፓትርያርኩን አምባገነናዊ አካሄድ ክፉኛ በመቃወም ፓትርያርኩ ሥልጣናቸውን እንዲቀነስና እንዲገደብ ታላቅ ትግል አድርገው የነበረው አቡነ ሰላማና አቡነ መልከጼዴቅ በጥቂት ግዜያት ውስጥ አረፉ "ብለው "ጉዳዩ የበለጠ አስገራሚ የሆነው ደግሞ ሁሉም የሞቱት ምግብ ተጋብዘው ከበሉ በውኋላ ባደረባቸው ከባድ ሕመም መሆኑ ነው"ይሉና "ያቡነ በርናባስ ፓትርያርኩን አጥብቀው መቃወምና ድንገተኛ እረፍታቸው"።

"ብለው የሌላውን ሊቀ ጳጳስ ስም ሲጨምሩ "የአቡነ ቄርሎስ ሽሽትና ምስጢራዊ ሕክምና"ብለው" የአቡነ ይስሃቅ ድንገተኛ ህክምና ሞት" ብለው ከጳጳሳቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዙረው የተገደሉትን ሲዘረዝሩ "የመጋቢ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ሚስጥራዊ አሟሟት "ይሉና "የጎንደሩ ሊቀ ሊቃውን ፓትርያርኩ አዲስ አበባ ለመጽሐፍት ትርጓሜ ተጠርተው አዲስ አበባ በደረሱ በጥቂት ቀናት በድንገት አረፉ ተብሎ አስከሬናቸው ተጫነ"ሲሉ ጽፈዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ተበተኑ። ቤተ ክርስቲያን በእሳት ተለብልበዋል። አብሮም በእስልምና ሃይማኖት እያመካኙ በደቡብ ኢትዮጵያ ብዛት ያላቸው ቤተ ክርስቲያናት የእሳት እራት ሁነዋል። ምዕመናን ተገደው ሰልመዋል ብዙ ብዙ ግፍ በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናን ላይ ደርሷል። ይህን አስመልክቶ ወያኔ መልምሎ በስለላ ያሰማራቸው የዛሬው ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ጳጳስ የክርስቲያኖችን መገደልና መሰቃየት በተመለከተ አምነውበት ይሁን ሳያምኑበት አይታወቅም ምስክርነታቸውን በመጽሐፍ ገልጸዋል።

አባ ሳሙኤል <u>በኢትዮጵያ የሃይማኖት መቻቻል አለን?</u>በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 26 “ለምሳሌ ጥቅምት 6 ቀን 1997 ዓም በአርሲ ዞን ኮልፌ ወረዳ ቆሬ ከተማ ከልዩ ልዩ ቦታ የተሰበሰቡ አክራሪ ሙስሊሞች አሥር ክርስቲያኖችን ገደሉ፤ሦስት በከፍተኛ ሁኔታ ቆሰሉ፤ 2237 ምእምናን ከአካባቢው ተነፋቀሉ፤አንድ ቤተ ክርስቲያን እና 194 የክርስቲያን ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተቃጠሉ፤24 የክርስቲያን ቤቶች በከፊል ተቃጠሉ። 304 የክርስቲያኖች ከብቶች ተዘረፉ” ይሉና ገጽ 27 “ጥቅምት 24 ቀን 1998 ዓም ከኢድ አል ፈጥር በዓል መልስ ክርስቲያኖች ይውጡልን እጃቸውን እንቆርጣለን እያሉ በቆሬ ኮልፌ በአይሱዝ መኪና ተጭነው መፈክር ሲያሰሙ ዋሉ”ይሉና“ ጉዳዩ በዚህ መልክ ቸል በመባሉ ሕዳር 7 እና 8 ቀን 1998 ዓም አላህ አክቡር እያሉ ከልዩ ልዩ ቦታ የተሰባሰቡ አክራሪዎች አንሻ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያንን አቃጠሉ፤ብዙዎችን ገድለው የ72 አባወራዎች ቤት አቃጠለ”ይሉና።

ገጽ 33 “የዚህ ሁሉ ችግር መንሥኤ አንዳንድ የመንግሥትንና የሕዝብን ኃላፊነት የተረከቡ ግለሰቦች አደራ በመዘንጋት የተረከቡትን ሥልጣን ተጠቅመው የሌላውን እምነትና ሥርዓት አጣጥለው የራሳቸውን እምነትና አመለካከት ከሌላው በላይ ለማሳደር ሲሉ የሚፈጥሩት ተጽዕኖ ስለሆነ ይህም ሊስተካከል የሚገባው ነው” ይሉና ገጽ 66 “ከሃይማኖት በቀር የዘርና የቋንቋ ልዩነት በሌላቸው ለረጅም ዘመናት ተከባብረውና ተቻችለው በአንድነት በሚኖሩ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች መካከል ቅራኔ እንዲፈጠር ፍላጎታችን አይደለም” ይሉና በገጽ 140 “ሱራህ 4.17/ እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ!በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ



ከእውነት ሌላ አትናገሩ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ቃሉም ነው”የሚለው ከቅዱስ ቁርዓይ ጠቅሰው ጽፈዋል።

ኤፍሬም እሸቴ <u>አክራሪነት በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 173 “ሴቶች ብቻቸውን ውኃ ለመቅዳትም ሆነ እንጨት ለመሰበር ወይም ከብት ጥበቃ ሲወጡ በሙስሊሞች ይደፈሩ ነበር። ከነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓም ጀምሮ ምዕመናን በግድ ማስለሙ ተጀምሮ ነበር። መስከረም 16 ቀን 1999 ዓም ጀምሮ የታየው ጭፍጨፋ ከዚህ ሁሉ በኋላ ከመምጣቱ አንጻር ዱብ ዕዳ ነበር፤ወንጀሉና ዕሊቂቱ እንዳይፈጸም ለማድረግም የማይቻል ነበር ማለት ያስቸግራል። በዚሁ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የአካባቢው ፖሊስ ኃይል መጀመሪያ ሊቆጣጠረው በሚገባው ወንጀል ከ18 በላይ ክርስቲያኖች ታርደው ተቃጥለው ሞተዋል። ከ38 በላይ በአሰቃቂ ኹኔታ ቆስለዋል። ከ488 በላይ በግዳጅ ሰልመዋል። ከ2.000 በላይ ተፈናቅለዋል። 3 አብያተ ክርስቲያናት (ማለትም በሻሻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቡሬ ቅዱስ ገብርኤልና ጩጎ ቅዱስ ገብርኤል) እና ከ850 በላይ ቤቶች ተቃጥለዋል”ሲሉ የደረሱትን ጉዳቶች ዘርዝረው ጽፈዋል።

<u>በጅማና በኢሉባቦር ክርስቲያኖች ሰማዕትነት ተቀበሉ</u> ተብሎ በድረገጽ የተለቀቀው ባለ 13 ገጽ መጣጥፍ የዓይን ምስክር ጠቅሶና በምስል ፎቶ አስደግፎ አውጥቶታል። ገጽ 1“ በጅማ ሀገረ ስብከት ጎማ ማና ቶባ እና በኢሉባቦር ሀገረ ስብከት በዴዴሳ ወረዳ መስከረም 16 ቀን ጥቅምት 4/1999 ዓም ሌሊት በአካባቢው አክራሪዎች ክርስቲያኖችን በገጀራ ባይፍና በጦር እየቆራረጡ በእሳት በማቃጠል አሰቃቂ ግድያ ፈጽመዋል። የኢሉባቦርና ጋምቤላ አህጉረ ሥራ አስኪያጅ እንደገለጹት በዴዴሳ ወረዳ የቤተ ክርስቲያን አካላት እንደሚናገሩት 800 የክርስቲያን ቤቶች ናቸው የተቃጠሉት ይላሉ። የመንግሥት አካላት ደግሞ ከ450 በላይ የግለሰቦች ቤት መቃጠሉን ስድስት ክርስቲያኖች በአሰቃቂ ሁኔታ መገደላቸውን 987 ምዕመናን ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በደንቢ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ተጠልለው እንደሚገኙ ገልጿል። የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ተቃጥሏል የጨሎ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ተቃጥሏል። በርካታ ክርስቲያኖች ቁጥራቸው ከ200 በላይ ተገደው የሰለሙ መሆናቸውንም ገልጸዋል” ሲል ጽፏል።

ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቃ የምትኖር በመሆኗ ወያኔ ልዩነት እንዲፈጠር ማድረግ ብቻ ሳይሆን አማኞች እንዲገደሉና እንዲሰደዱ የማስተማሪያ ቦታዎች በእሳት እንዲነዱ በማድረግ ምዕመኑ በሃይማኖቱ ተስፋ ቆርጦ ወያኔ ያለውን እንዲከተል ለማድረግ ነው። ለዚህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ይህን ያህል ጥፋት አድርሷል። በአንድ ሳምንት 3 ታላላቅ ገዳማት ተቃጥለዋል። በአንድ ሳምንት ጎንደር ከተማ 2 ታዋቂ ትምህርት ቤቶች እሳት በልቷቸዋል። ጎጃም በአንድ ሳምንት 8 ቤተ ክርስቲያኖች ወድመዋል።

የቤተ ክርስቲያን ቅርሳቅርስ በመጀመሪያ ተዘርፈው ከዚያም በሳት ጋይተዋል። ታላላቅ ገዳማት በስኳር ምክንያት ታርሰዋል። መምህራን አገር ጥለው ተሰደዋል። ጳጳሳት ብቻ ሳይሆን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ በመጀመሪያ ከሥልጣን አውርደዷል። ከዚያም አገር ጥለው እንዲሰደዱ አድርጓል። ከዚያም ስደተኛው ሲኖዶስ ተቋቁሞ ሕዝብ አስተሳስሮ ለመያዝ ጥረት ማድረግ ተጀመረ። ይህ በዚህ እንዳለ አንዳንዶቹ ከልባቸው ሌሎች ለጥቅማቸው ሲሉ የተከፈለችውን ቤተ ክርስቲያን ለማስታረቅ ሞከሩ። የቤተ ክርስቲያን አንድነት የማይወዱት አቶ ስብሃት ነጋ አስፈራሩ።

አቶ ስብሃት ነጋ ሳይፍ መጽሔት ጥር 2005 ዓም "እርቅ ለመፈጸም በማለት ሰዎችን ሲልኩ የነበሩ ቄሶች መስቀል አለባቸው። ዕርቅ ከነዚህ ጋራ መደረግ የለበትም"ሲሉ ተናግረዋል። ሌላው ቀርቶ ስደተኞች ጳጳሳትን ወደ ኢትዮጵያ ተይዘው እንዲሰጡአቸው ብፁዕ ወጣዮት አቡነ ጳውሎስ ለአሜሪካ እምባሲ መናገራቸው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ምኒስትር ወይም እስቴት ዲፓርትመንት የተላከው መልዕክት ማስረጃ ነው። የዊክሊክን ሰነድ ወደ አማርኛ አቢይ አፍወርቅ ተርጉመው በድረገጽ አስነብበውናል።

ትርጉም አቢይ አፍወርቅ "የአዲስ አበባዋ ቤተ ክርስቲያን በኢምባሲያችን በኩል የአሜሪካ መንግሥት ርዳታ ለመጠየቅ ማሰቧን ተረድተናል። በአሜሪካ ያለው ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ስም መጠቀም እንዳይችል እንድናግድላቸውና ዋና ዋናዎቹን የቤተ ክርስቲያኗን ሀላፊዎችም ወደ ኢትዮጵያ አስገድደን እንድንመልስላቸው ይፈልጋሉ"ይላል። በስደት ያሉትን አባቶች ወደ ኢትዮጵያ



ለመውሰድ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ ሲሆንባቸውና በኢትዮጵያ ስም ቤተ ክርስቲያን እንዳይከፍቱ ለማድረግ ያቀዱት እቅድ የማይሆን መሆኑን ሲያውቁ ደግሞ በሕዝቡ መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ጥረዋል። በተለይ ዲያስፐራውን ቤተ ክርስቲያን በዘር እየለያዩት እንደሆነ በእስር ያሉት አቶ አንዱዓለም አራጌ አብራርተዋል።

አንዱዓለም አራጌ ያልተሄደበት መንገድ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 200 "ኢትዮጵያውያን በዓለም ዙሪያ ተበትነው በሚኖሩባቸው ሀገሮች ሁሉ በደርግ ጊዜ እንኳን ፈጣሪን በአንድ ጣራ ሥር ሁነው ያመልኩ ነበር። ለሀገራቸውም ተማጽኖን በጋራ ያቀርቡ ነበር። በዘመነ ኢሕአዴግ ግን የሆነው ፍጹም ከዚህ የተለየና ቅስምን የሚሰብር ነው። እግዚአብሔር እንኳን ኢትዮጵያውያንን የዓለምን ሕዝብ ሁሉ እኩል እንደፈጠረ ሁሉም ጠንቅቀው እያወቁ እግዚአብሔርም አንድ ሆኖ ሳለ የየብሔሩ እግዚአብሔሩን ፈጠሩ። ፈጣሪ በፍጡሮቹ ተፈጠረ። ኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች ከወንድምና እህቶቻቸው ጋር ለዛውም በስደት ሀገር ችግሮቻቸውን ሳይፈቱ በልባቸው ጥላቻና ቂምን አዝለው በየቀለሷቸው ቤተ ክርስቲያኖች ፈጣሪን ለመማፀን ሰንበትን ይጠብቃሉ።"

"ይህ ጉዳይ በዋናነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት አማኞች ዘንድ በጉልህ የሚታይ ነው። በሌሎች እምነቶች ተከታዮች ዘንድ በእርግጥ ይኸ ጉዳይ መንፀባረቁን አላውቅም። አንባቢዎች እንድትረዱልኝ በትህትና የምጠይቀው የሁሉም ነገር ልዩ ሁኔታዎች እንዳሉት ሁሉ አሁን በምንወያየው ሁኔታም ላይ ቢሆን በደምሳሳው የዚህ የዘረኛነት ቫይረስ ሰለባዎች ናቸው ብዬ እየተከራከሩኩኝ አለመሆኑን ነው። ነገር ግን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረውና የእምነት አባቶችን ላይ ችግርን እንደፈጠረ መረዳት እንችላለን። የህወሓት/ ኢሕአዴግ አገዛዝ በዋናነት የአገዛዝ መሠረቱን በዘር መደላደል ላይ ያዋቀረ በመሆኑ ችግሩ ከድጡ ወደ ማጡ መውረዱ አልቀረም። ሁሉን ነገር ከልዩነት የሚጀምር ለኢትዮጵያ ታሪክ ክብር የማይሰጥ ከአፈሙዝ ባገኘው ሥልጣን ኢትዮጵያውያንን በእመለካከት ሳይሆን በቀለሰላቸው የዘር ጎጆዎች የሚሰድር አገዛዝ መገናኛ ብዙሃኑንም ሁሉንም ተቆጣጥሮ ሌት ተቀን ስለዘር ልዩነት ሲሰብክ ሕዝቡ ላይ የሚወድቀው ሸክም ቀላል አይሆንም"ሲሉ ጽፈዋል።

የኢትዮጵያ አንድነት ስም የያዘ ተቋም እንዳይኖረው ለፍቷል። ለዚህም ተሳክቶለት የኢትዮጵያ አስፖርት ፌዴሬሽን ከሁለት ከፍሏል። በቤተ ክርስቲያንም ቢሆን የእርሱን አቋም የማይቀበሉትን ቅድሚያ ካህኑን በጥቅም ይይዛል። የካህኑ አማካሪዎች ሁነው የሚመደቡት ነጋዴዎችን አስገብቶ አንድነታቸውን እንዲያጡ ያደርጋል። ለምሳሌ በገለልተኝነት ሁና የአዲስ አበባውን ሲኖዶስ ድክመት ትዋጋ የነበረች ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮን ማርያም ነበረች። ይችን ቤተ ክርስቲያን ለመውረስ ወያኔ ያደረገውን በድረገጽ የሚለቀቀውን መግለጫ መመልከት ይቻላል።

<u>በሀገረ እንግሊዝን ሆነ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ለምትገኙ</u> የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች የተባለው መጣጥፍ ገጽ 19 " በወያኔ ኢሕአዴግ ገንዘብ ተጠቅመው የሴኩሪቲ ኃይሎችን በማጠናከር አባላትን ከግቢአቸው ለማገድ ስለሚሞክሩ በመላው ዩኬ የሚገኙ የቤተ ክርስቲያኑ አባላትና ተገልጋዮች መላው ነጻነት ወዳድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ስደተኛ ሁሉ በየዕለቱ በርዕሰ አድባራት ለንደን ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመገኘት ለነጻነታቸው፤ለመብታቸውና ለእውነት መቆም ይኖርባቸዋል።"

"እነዚህ ሕዝብን የካዱና ስደተኛውን ኢትዮጵያዊ በመስደብና በማዋረድ ሃብትና ንብረቱን ቀምተው ለመጣል የኢትዮጵያን መንግሥት ወያኔ ኢሕአዴግ ኢምባሲና ሀገር ስብከት መተማመኛ ያደረጉ ወገኖች በዩኬ የጀመሩት ተግባር ተሳካላቸው ማለት በመላው ዓለም በሚገኙ ኢትዮጵያኖች ላይ በመዝመት መብታቸውንና ነጻነታቸውን ለመግፈፍ ቻሉ ማለት ስለሆነ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለንደን ማርያም ቤተ ክርስቲያን አባሎች የሚያደርጉትን ትግል በጸሎታቸው እንዲያስቧቸው"ሲሉ ተማጸኑ።

ስለዚህ መገንዘብ ያለብን ነገር ቢኖር እያንዳንዱ ከኔ ካልደረሰ ብሎ መጠበቅ የለበትም። የለንደን ወገኖቻችን በቻልነው መጠን ልንተባበራቸው ይገባል። ዝም ማለት ያለብን አይመስለኝም። ምክንያቱም የጥቅም ሰዎች እንደሰደድ እሳት አንዴ በያለንበት መጥተው ሰላም ይነሱናል። ግለሰቦች ኢትዮጵያ ቤት የሰሩና ንግድ መሬት የተቀበሉ ከግማሽ በላይ ማለት ይቻላል ባልንጀሮቻቸውን የያዙትን አቋም እንዲተው መንገር እንዳለባቸው ታዘዋል። በዚህ



ምክንያት ዋሽንግተን ዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የመሸገው የወያኔ ቡድን ሰላም ነስቶ ቤተ ክርስቲያኑን በመጀመሪያ ከፍሏል። አሁን ደግሞ ሲኖዶሱን ከፍሎ ሊያጠፋ እየለፋ ነው።

ስደተኛውን ሲኖዶስ ለመበተን የታቀደው ሕዝቡ ወያኔን በግድ እንዲደግፍ ለማድረግ ታስቦ ነው። ብፁዕ ወጣየት አቡነ ጳውሎስ አቅም አጥረቸው እንጂ ቅዱስነታቸውን የአሜሪካ መንግሥት ይዞ ቢሰጣቸው ደስ ይላቸው ነበር። ይህ ባለመሳካቱ ርካታ ሳያገኙ ከዚህ ዓለም ተሰናብተዋል። የወያኔው መንግሥት ግን እርሱ በሚያዛቸው በጉዳይ ፈጻሚወች በኢምባሲው በኩል ከዚህ በፊት መመሪያ ብሎ የላከው ሠነድ ምስክር ነው። ይህ በመንግሥት የታዘዘው በውጭ አገር ያሉትን ማንኛውም ድርጅት ለወያኔው ኢሕአዴግ ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በየእምባሲው የተላከው መመሪያ ያስረዳል።

<u>በውጭ አገሮች በሚገኙ ሚሲዮኖቻችን የኮንስትወንሲ ግንባታ የሚመራበት ማንዋል</u> መመሪያ ገጽ 6 "ኢትዮጵያውያንን ያሰባሰቡ ማህበራት፤የሃይማኖት ተቋማት የሙያ ማህበራት ወዘተርፈ"ብሎ የሚገልጸው እነዚህን ድርጅቶች በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጣል። ምን ይህ ብቻ ሌላም መመሪያ ተላልፏል። ያም ለወያኔው መንግሥት አልታዘዝም የሚለውን ግለሰብ ስም በማጥፋትና አሉባልታ በማውራት ጥገኝነት ጠይቆ ከሚኖርበት አገር መንግሥት ጋር ቀርቦ ወንጀለኛ መሆኑን ማስረዳት እንዳለባቸው ለኢምባሴዎች የተላከው በውብሸት ደምሴ/ አምባሳደር በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ዋና ዳሬክተር ተብሎ የተጻፈበት ባለ 37 ገጽ አለ።

<u>ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ቋሚ.መልዕክተኛ ጽ/ቤት ቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤት በያሉበት</u> የተባለው መመሪያ ገጽ 8 "የአክራሪውን ተቃዋሚ ጎራ ለማዳከም እንዲረዳ በውጭ አገሮች ያሉ ቀንደኛ አስተባባሪ የሆኑ አባላትን በመለየት ዝርዝራቸውን ለዋናው መ/ቤት ማስተላለፍ" ይላል። በዚህ ምክንያት ስደተኛውን ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ በማቋቋም የሚታወቁት ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ መሆናቸውን ወያኔ ያውቃል። ከዚያም የአገሩን ስርዶ በአገሩ በሬ እንዲሉ እኔ ከተወለድኩበት ወረዳ መመልመል ተጀመረ። ወይዘሪት

አዜብ መስፍን ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል የተማሩ ደብረታቦር ነው:: እርሳቸው የክፍል ባልንጀሮቻቸውን በጥቅም አደራጅተዋል::

ከዚያም ስደተኛውን ሕዝብ አንድ አድርጎ የሚይዝ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን መሆኑን ብቻ ሳይሆን ጥር 13 ቀን 1999 ዓም ጳጳሳት የሾመበት ቤተ ክርስቲያን ነው:: ይህ ቤተ ክርስቲያን ቁልፍ መሆኑን በማወቅ ችግር ከዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዲነሳ አድርጓል:: የደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲያጣና ችግር እንዲፈጠር ከተደረገ ወዲህ በአንዴ እንደሰደድ እሳት በየቤተ ክርስቲያኑ ችግር እንዲነሳ ሁኖአል:: በትክክል በጥናቱ መሠረት ተሰርቷል::

አንድ ነገር ማወቅ ያለብን ጉዳይ ቢኖር ዛሬ ወያኔ ማለት ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪው ብቻ አይደለም:: በተለይም ወጣቱን በጥቅምና በተለያዩ ቁሳቁስ አደንዝዞታል:: ወያኔው እቅድ ያወጣል ፈጻሚው ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጎሳ አውቆት ወይም ሳያውቅ የገባው ይፈጽማል ይህን ነው ጠንቅቀን ማወቅ ያቃተን:: ወያኔ አራት ኪሎ ቁጭ ብሎ አጥንቶ የሚልከው ነው ዛሬ የሚፈጸመው:: ለዚህም በብዛት ሆዳቸው አምላካቸው የሆኑትን በመያዙ ተቃዋሚውን ኃይል አዳከሞ ሲያበቃ አሁን ደግሞ ወደ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አይኑን አፍጥጦ ጥርሱን አግጦጦ መጣ::

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ በሚያወጣው መግለጫ ወያኔ ሆነ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ የሚፈጽመውን ግን ማጋለጡን አጠንክሮ ገፋበት:: ይህ ለአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሳይሆን ለአራት ኪሎው የምክር ቤት መርዝ ሁኖ ታያቸው:: እነሱ ሰላም ነው የሚሉትን ሰላም አለመኖሩን ደግሞ ደጋግሞ መግለጹ ተንገበገቡ ምክንያቱም ወያኔ ከምንም ይልቅ የሚጠሉት ዋናው እውነት የያዘን ድርጅት ወይም ግለሰብን አይወድም:: ባላቸው አቅም ለማጥፋት ይጥራሉ:: ለዚህ ሳይሆን ይቀር እንዴ ሉቃስ 9፤23"በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ"እንዳለው ወያኔም በቤተ ክርስቲያን ላይም ያፍራል:: ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ትውልዱ እንዳያፍር የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና የኢትዮጵያን አንድነትን አጠንክሮ መግለጫ አውጥቷል:: እስኪ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አገርንና ሕዝብ ቤተ ክርስቲያንን አስመልክቶ ያወጣውን መግለጫ በእጄ ካለው እንመልከት::



# ምዕራፍ 4

## ስ/ሲ/ሊጠቃ የቻለበት ምክንያት በአጭሩ ሲዳሰስ

ስደተኛው ሲኖዶስ ከተመሠረተ ጀምሮ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የማያወላውል አቋም ያዘ:: ወያኔ ከአገር ውስጥ ያለውን የሕዝብ ይግባኝ ሰሚ የነፃውን ፕሬስና በሥነ መንግሥት በፖለቲካ ድርጅት የተሰባሰቡትን ተራ በተራ አጠቃ:: በዚህ ሰዓት ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተ ክርስቲያን ሆነ በመንግሥት ብሎም በጎሳዎች ላይ የሚደርሰውን ጥፋት ተከታትሎ ማጋለጥ ተግባሩ ሆኑ::

ይህ ብቻ አይደለም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 12፤26" እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም "ብሎ ያስተማረውን ትምህርት በስደተኛው ሲኖዶስ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ማስተማር ተግባሩ ሆነ:: እንደ አዲስ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ አየነቱ ያለ ምንም ክፍያ ሰበኩ:: በተለይ እርሳቸው ቅድሚያ በማህበረ ቅዱሳን ይሳደዱ ጀመር:: ዛሬ በተረዳሁት መሠረት ማህበረ ቅዱሳን በሦስት ይከፈላል::

1ኛ አድርግ ወይም ተሳደብ ሲባል የሚያደርግ የሚሳደብ
2ኛ ከእኔ ሌላ የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኝ የለም የሚል
3ኛ የሰማውንና ያነበበውን ይዞ የሚያራግብ ቡድን ነው::

ከሁሉም ብሶ ሰላም የነሳው አድርግ የተባለውን የሚያደርገው ቡድን ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል 9፤37" መከሩስ ብዙ ነው፤ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው"እንዳለው በዓለም ዙሪያ የተበተነው ሕዝብ ለመሰብሰብ የተደረገው ጥረት ወያኔን አስደነገጠ:: ስደተኛው ሲኖዶሱም በቤተ ክርስቲያን በገዳማትና በአድባራት ላይ የሚደርሰውን ችግር አስመልክቶ በሰፊው ማስተዋወቅ ጀመረ:: ከዚህ በታች በትንሹ ከእጄ ባለው መረጃ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ያወጣቸውን መግለጫዎች አጠር አድርጌ ጥቅስ ልጥቀስ::

በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጽፈት ቤት የተሰጠ መግለጫ ገጽ 1 "ታሪካዊ የሆነችው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በፍትሕና በእውነት ጎዳና ለመምራት ከጌታና ከሐዋርያት ደግሞም ከአበው አደራውን የተቀበለው ቅዱስ ሲኖዶስ በነጻ ፕሬስ አባላት፣ በፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና እና በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ላይ የተሰጠው ፍርድ ለሀገር አንድነትና ሰላም እንቅፋትና ሀገራችንን ወደ በለጠ የእርስ በእርስ ግጭት የሚመራ ስለሆነ ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖች ሁሉ ወደ እርቅና ሰላም እንዲመጡ ጥሪ በማቅረብ የታሰሩ የፖለቲካና የኅሌና እስረኞች በሙሉ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ፤ የመሰብሰብና የመናገር መብት ከሰው ልጆች የማይገሰስ ነጻነታቸው ስለሆነ ያለፈውን ምርጫ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ የወጡትን ኢትዮጵያውያን የገደሉና አካለ ጎደሎ ያደረጉ የጸጥታ ኃይሎችና ትእዛዝ ያስተላለፉ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲጠየቁና በሥልጣን ያለውም ፓርቲ ኃላፊነቱን በይፋ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠይቅ"ሲል በሰፊው የአገሪቱን ችግር ዘርዝሮ አውጥቷል:: ዓመትና ቀን የለውም::

<u>ሚያዝያ 19 ቀን 2005 ዓም በአገራችን በኢትዮጵያ በአማርኛ</u> ተናጋሪ ወገኖቻችን ላይ እየተካሄደ ያለውን የዘር ማጽዳትና ማጥፋት ዘመቻ አስመልክቶ ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ በሚል "የኢሕአዴግ መንግሥት አገራችንን ኢትዮጵያን በጠመንጃ ኃይል ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ ግን ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ከባድ አደጋ ውስጥ ይገኛል:: አገሪቱን በዘርና በጎሳ በመሸንሸን አንዳች ችግር ቢፈጠር በአንድነት አገራዊ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ እንዲበታተኑ የሚያደርግ የጎጥ ፖለቲካ በሕገ መንግሥቱ ላይ ቀርጾ አስቀምጧል:: ይህን ያደረገው የራሱን እድሜ ለማራዘም ነው:: በዚሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሰብአዊ መብት ጥሰት የመልካም አስተዳደር እጦት እና የኑሮ ውድነት እየጨመረ መምጣቱ የሚታወቅ ነው::"

"የዘር ማጥፋት ዘመቻውንም መልኩን በመቀያየር በቦረናና በአርባ ጉጉ፣በጋምቤላና በኦጋዴን፣ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በአፋር፤ በደቡብ ኢትዮጵያና እና በቤኒሻንጉል በሚኖሩት ወገኖቻችን ላይ በመከናወን ላይ ነው:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህ እየተከናወነ ያለው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ጥቂቶች በብዙዎች ላይ ነግሠው እንዲኖሩ ለማድረግ የታቀደና የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ በመላው ዓለም ያለን ሕዝቦች የወገኖቻችንን ግፍና ስቃይ ሰቆቃ ተረድነት ጩኸታችንን በማሰማት ድምጽ



ለታፈነበትና በሰቆቃ ላለው ሕዝብ ድምጽ በመሆን በዓለም የተለያዩ መድረኮች ጩኸቱን እንድናደርስለት ጥሪ ታቀርባለች"ይላል የጽፈት ቤቱ መግለጫ::

<u>የቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ</u> ጥቅምት 2003 ዓም ገጽ 2 "በተለይም በውጭው ዓለም የተወለዱ ወይም በሕጻንነታቸው ካገራቸው የወጡ ታዳጊ ወጣቶች ሃይማኖታቸውንና ባህላቸውን በሚገባቸው ቋንቋ ካልተማሩ ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው እየራቁ ስለሚመጡ አፋጣኝ የሆነ መፍትሄ መፈለግ እንዳለበት ጉባኤው አምኖበታል"ይላል መግለጫው::

<u>የሲኖዶስ ውናሴ መግለጫ</u> ግንቦት 2004 ዓም ገጽ 2 "ታላቁ የዋልድባ ገዳማችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በሀገራችንም ብሔራዊ ታሪክ ውስጥ እንደ ከዋክብት የደመቁ ታላላቅ ቅዱሳንን ያፈራ ገዳም ነው:: ዛሬ ግን ሀገርን ለማልማት በሚል ሰበብ የገዳማቱን ታሪክ ሳይጠና እና በቦታው ያሉትን ቅዱሳን አባቶች ምክር ሳይጠየቅ በማን አለብኝነት ገዳማቱን በማፍረስ ሊሰራ የታቀደው የስኳር ፋብሪካ የልማት ሳይሆን የመርገም ፋብሪካ እንደሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ ያምናል:: የቅዱሳን ጸሎት እንኳን ከስኳር ከወርቅና ከአልማዝ የሚበልጥ በረከት ነው::"

"በመሆኑም በህያዋኑ ላይ ስደት በቅዱሳን አጽም ላይ ፍልሰት ያመጣውንና የወያኔ መንግሥትን ድርጊት ቅዱስ ሲኖዶስ በጽኑ ያወግዛል:: በመሆኑም የወያኔ ባለሥልጣናትም ከዚህ አፍራሽ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ መላው ሕዝበ ክርስቲያን የማንነቱና የክብሩ መለያዎች የሆኑ ገዳማት መደፈር የእርሱ መደፈር መሆኑን በማወቅ አቅሙ በፈቀደ መጠን የተቃውሞ ድምጹን እንዲያሰማ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪ ያቀርባል"ሲል ጠንከር ያለ መግለጫ ጽፏል::

<u>ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ</u> 04/04/12 የወጣው ዋልድባ ገዳምን አስመልክቶ ገጽ 2 "ገዳማቱ የዘር ክፍፍልን አያውቁም፣ገዳማቱ የቋንቋ ልዩነትን እንደ ዘር ወስደው አይለያዩም፣የወያኔ ካድሬዎች ካልሆኑ በቀር ገዳማውያኑ ከሰው ሰውን አያበላልጡም፣እንዲያ ቢሆንን ኖሮ አቶ መለስ የአክሱም ሐውልት ለወላይታው ወይም ለደቡብ ሕዝብ ምኑ ነው ባሉ ጊዜ ወይም የዚያ ክልል ገዳማት መነከሳት በመላ ኢትዮጵያ ባሉት ገዳማት አይኖሩም ነበር፣የመላ

አውስትራልያ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ወደ ስደተኛው ሲኖዶስ እንዲቀላቀሉ አድርገዋል:: በነዚህም ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅና ሌሎች ጳጳሳትም እንዲሄዱ ያደረጉ አባት ብፁዕ አቡነ መልኪቀዴቅም በስራቸው ተደስተው ቅዱስ ሲኖዶሱ "አዲስ ሐዋርያ"ይባሉ ብለው ማዕረግ አሰጥተዋቸው ነበር:: ዛሬ ግን የዲሲው ቡድን ባቀነባበረው ሴራ ያከበሩአቸውን አባት መልሰው ሲያጣጥሏቸው አድምጠናል:: ደቡብ አፍሪካ ጆሓንስበርግ ቅ/ስላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን የወጣው መጣጥፍ እንዲህ ይገልጸዋል::

ተክለ ማርያም በደረ ገጽ <u>ሁለቱ ድንቅ ሐዋርያዎች</u> በሚል መጣጥፍ "በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፀሐፊ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በቦታው በመገኘት የመረቁት ሲሆን ከእርሳቸው ጋር በዚህ ዘመን በአገልግሎታቸው በስጦታ ፀጋቸው ወደር የማይገኝላቸው ራሳቸውን ለክርስቶስ ወንጌል ሰጥተው በህይወቱ ውስጥ እየኖሩ የሚያስተምሩ እውነተኛ የክርስቶስ ሐዋርያ ለመንጋው የሚጨነቁ የሚኮንናቸውን የሚመርቁ የትህትና፤የትግሥት ስጦታ አባት ታላቁ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሳኤ እንዲያው የሚያደንቀው ነገር ትንሽ ባስታውስ አንዳንድ ሸክማቸው የከበዳቸው::"

"የግብር አባታቸው መግለጫ የሆኑ የወንጌልን ትምህርት ለማጸከም ምዕመናንን ለማሰናከል ከንቱ ድካም በአሉባልታ ለፈተና መራወጣቸውን ብናስታውስ ያሁሉ ፈተና ግን በአባታችን ላይ ሳይገለጥ ጥላ ሆኖ አልፎ እንደሐማ እጣው ለእነሱ ሆነባቸው:: በተለያዩ ግዜ የእግዚአብሔርን ስራ አይተንበታል"ሲሉ ጽፈዋል:: ከዚህ ላይ ሊረሳ የማይገባ ነገር ቢኖር የዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ እጥረት እንዳይኖረው የጣሩ ሐዲስ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሣኤ ናቸው::

<u>አቶ ፍስሃ ማንጠግቦት</u> "አባ ወልደ ትንሣኤ ለቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከ150 ሺህ ዶላር በላይ እንዲዋጣ ያደረጉ አባት ናቸው" ብለውኛል:: አቶ ፍስሃ እንዳሉት ኋላማ ሳጣራ ድምጻውያን አሰባስበው ያን የመሰለ ያሬዳዊ ዜማና መዝሙር እንዲታተም ያደረጉት እርሳቸው ናቸው:: ታዲያ አባ ወልደ ትንሣኤ፤ ዲሲ ገብርኤል "አትግባ"መባል ነበረባቸው? ብር ባለበደ ጠጠር መልስለት ሆነና እንደ ወንበዴ በበፖሊስ ታሰሩበት:: አምናለሁ አምላክ ፈቃዱ



ሁኖ አንድ ቀን በፖሊስ የታሰሩበት ቤተ ክርስቲያን እርሳቸውን እንዲጠላ የተቀሰቀሰው ምዕመን ባለበት ገብተው የሰላም ቃል ያስተምሩታል የሚል እምነቴ ነው:: በዚህ ቀን እርሳቸው ታስረው ሲወሰዱ የታዘቡትን ጽፈው በድረገጽ አስነብበውናል::

ታዛቢ <u>ከቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን</u> ጹሑፍ ገጽ 2" ቤተ ክርስቲያንን እያመሰ ያለው ዶ/ር ነጋን ከስር መሠረቱ ለማወቅ ያህል መራሹ የወያኔ መንግሥት ወደ አዲስ አበባ እንደገባ ወያኔን በሀቡእ የሚዋጋ ድርጅት አፍርሶ ለወያኔ ገጸ በረከት አቅርቦ በአጸፋው ወያኔ የነጻ ትምህርት እድል በአውሮፓ ሰጥቶታል፤ወደ ሀገር ቤትም ተመልሶ በቀድሞ ቴሌኮሚኬሽን አገልግሎት የማሰልጠኛ ክፍል የዲያሬክተርነት ሥልጣን ተሰጥቶት ከቀድሞ ኢንፍራስትራክቸር ሚኒስትር አሁን በብራስልስ አምባሳደር ዶ/ር ካሱ ኢላላ ጋራ ጥሩ ወዳጅ ነው"ሲሉ ጽፈዋል::

<u>አቶ ዘመድኩን</u> የተባሉ ግለሰብ ሊቅ ዶ/ር ነጋ ከወያኔ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዳላቸው በቁጭት ተናገሩ:: ይህን የሰሙ ሰዎች ሰፋ ያለ ዘገባ እንዲያቀርቡ ቢጠየቁ አቶ ዘመድኩን ፈቃደኛ አልሆኑም:: ምክንያታቸው "የጠፋው ጥፋት ላይመለስ ይቅር" ብለው ትተውታል ግን ለወያኔ ጥሩ የስሩ መሆናቸውን በመጀመሪያ ቀን ተናግረው ነበር እርሳቸው የተናገሩት ታሪክ ከዚህ ዝቅ ብሎ ከምጠቅሰው ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው:: አቶ ዘመድኩን የሚኖሩት አውስትራልያ ነው::

ታዬ ብርሃኑ <u>ስደተኛው ቅዱስ ሲኖዶስ ተጋርጦበት ከነበረው አደጋ አመለጠ</u> ብለው በጻፉት ጹሑፍ ገጽ 3 "ዶክተር ነጋ ዓለማየሁ የሚባለው ግለሰብ በአሁኑ ጊዜ የዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ቦርድ ሊቀ መንበር ነው:: ዶ/ር ነጋ የወያኔ መንግሥት ለከፍተኛ የነጻ ትምህርት ዕድል ሰጥቶት ወደ አሜሪካ ልኮ ያስተማረው ሲሆን በኢሕአዴግ የአመራር እርከን ከፍተኛ ሥፍራ ላይ እንደነበረና መሥራት አልቻልኩም በሚል ሰበብ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ እንደመጣ ለማወቅ ተችሏል:: ገና ማንነቱ በቅጡ ሳይጠና በአፈ ጮሌነቱ እንዲሁም ደግሞ በሠፈር ልጅነት ምክንያት በሚገርም ፍጥነት በዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የቦርድ አመራር ውስጥ ቁልፍ ቦታ ሊያገኝ ችሏል::"

“ይህ ሰው እንደበቱን አለስልሶ የማያውቀውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለማስተማር አውደ ምሕረቱንም የሚደፍር ለውሸቱ ለከት የሌለው የዋህ ምዕመናንንና አንዳንዶችን በውዳሴ ከንቱ እየጠለፍ እንደፈለገ እየነዳቸው እንደሆነ ብዙዎች ያውቃሉ:: ይህ ግለሰብ በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ ያስከተለውን መዘዝ በመረዳት የዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን ነቅተው እንዲጠብቁ አደራ ተጥሎባቸዋል::”

“በአሁኑ ሰዓት ስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሕዝብ ይዞ በመገኘቷ የወያኔን ትኩረት ከሳበች ውላ አድራለች:: ለዚህም በተለያዩ ቦታዎች ወያኔ ካድሬዎችን እያስገባች ሕዝብና ቤተ ክርስቲያንን ለመከፋፈል ከፍተኛ ስልት ቀይሳ እየሠራችበት እንደምትገኝ ሁሉም የሚያውቀው ነው:: በብርሃን ፍጥነት በዲሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የቦርድ አስተዳደር ኃላፊ ዶ/ር ነጋ ዓለማየሁ የዚህ የኢሕአዴግ ስትራቴጂ አካል ሊሆን እንደሚችል በቅርቡ በቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን የፈጸመው አፍራሽ ክስተቶች ጠቋሚ ምስክሮች ናቸው”ሲሉ ጽፈዋል::

አባ ሰላማ <u>ድረገጽ በስደተኛው ሲኖዶስ ሥር የሚገኙ ሰባክያን ወንጌልን</u> የማጥቃት እንቅስቃሴው ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው በሚል በፈረንጆች ታህሳስ 18 ቀን 2013 የወጣ ሁሉፍ ነበር:: በወጣው ጹሁፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት እንዲህ ይላል::“የወያኔው ዶ/ር ደብረ ጽዮን የላከው ዶ/ር ነጋ አለማየሁ፣አቡነ መልከ ጼዴቅን በደካማ ጎናቸው ገብቶ የመበታተን ተልዕኮ እያከናወነ ነው”ይላል:: ሌላው አስተያየት ሰጭ “አልሰማችሁም እንዴ ዶ/ር ነጋ እኮ ትውልዱም ከትግሬ ነው:: ቋንቋውንም አቀላጥፎ ይናገራል”ይላል:: በእውነቱ ከሆነ ሊቅ ዶ/ር ነጋ ትውልዳቸው ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ጎንደር ሲሆኑ እስከ 12ኛ ክፍል ደብረታቦር የተማሩ ናቸው:: ተግባራቸው ግን ልክ ነው ወያኔ ያሰኛል:: ያለ ቦታው ሰውን ወስዶ ማስቀመጡ ትክክል አይደለም:: ወያኔን የምንጠላው እኮ በተግባሩ እንጂ ትግርኛ ቋንቋ በመናገራቸው ከቶ አይደለም:: ቅድሚያ ይህን ለይተን ማወቅ ያለብን ይመስለናል::

<u>አባ ሰላማ ድረገጽ</u> “አንዳንድ ምንጮች ደግሞ ኢሕአዴግ ወይም ማህበረ ቅዱሳን ወይም በራሱ ተነሳሽነት የሲኖዶሶች የእርቅ ኪሚቴ የሆነው የነ ሊቀ ካህናት ኃ/ሥላሴ እጅ አለበት ሲሉ አንዳንዶች



ምንጮች ደግሞ ስደተኛውን ሲኖዶስ ወክለው የእርቅ ኮሚቴ አባል የነበሩና ማህበረ ቅዱሳንነት የሚጠረጠሩት የዲ.እንዱዓለምና የአባ ጽጌ ድንግል ደገፋው እጅም ሊኖርበት እንደሚችል ጠቁመውናል” ይላል:: በእርግጥ ከአስታራቂዎች መካከል ቀሲስ አንዱዓለም ይርዳው የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ካህን ናቸው:: ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ በሽምግልናው ወቅት በግድ ተባርሬአለሁ ያሉት አሁን ደብዳቤ ተልኮልኛል ብለው አዲስ አበባ ደርሰው መጥተዋል::

ቆመስ አባ ጽጌ ድንግል የስደተኛው ሲኖዶስ አባል ናቸው:: ሉስ አንጀለስ ባሉ ምዕመን ዘንድ ደግሞ “ግሪክ ደርሼ መጣሁ ብለው አዲስ አበባ ሕደው መመሪያ ተቀብለው ተመልሰዋል”የሚሉ ብዙ ናቸው:: ቀሲስ ፋሲል የአዲስ አበባ ሲኖዶስ ደጋፊ ሲሆኑ የማህበረ ቅዱሳን ሊቀ መንበር እንደነበሩ ይነገራል:: ከዚህ በላይ ደግሞ የሊቅ ዶ/ር ነጋ አለማየሁ አንዳንዶች “ትንሽ ወንድም ናቸው”ሲሉ ሌሎች ደግሞ “ቅርብ ዘመዶች ናቸው” ይላሉ:: ወያኔ በግራም ሆነ በቀኝ ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ ለማፍረስ አልገባም አይባልም:: ወያኔ ይህን ያደረገው አዲስ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሣኤ ተዘዋውረው ምዕመኑ አስተምረው ወደ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ማስገባታቸውን ባለመፈለጉ ነው::

<u>በስደት ላይ ከሚገኘው ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ</u> መግለጫ ሚያዝያ 23 ቀን 2002 ዓም “አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ በአውስትራልያና በአፍሪካ በመካሄድ ላይ ያለው የስብከት ወንጌል ሐዋሪያዊ ጉዞ እንዲቀጥል ወስኗል:: ሌሎችም መምህራንም በሐዋሪያዊ ጉዞው እንዲሳተፉ መመሪያ ሰጥቷል”ይላል:: ወያኔ በተለይ ግንቦት 2002 ዓም ምርጫ ድል አድርጌአለሁ ብሎ በዓለም ላይ ጮኸ:: በሳምንቱ መቀሌ ዝግ ስብሰባ አድርጎ ዲያስፖራውን ለመበታተን $40 ቢልዩን ዶላር መደበ:: ወር ሳይሞላ ሳንሆዜ በነበረው የኢትዮጵያውያን እስፖርት ፌዴሬሽን ከሜዳው ላይ አምባሻ ሰንደቅ ዓላማ ለመስቀል እንዲቻል ብዙ ገንዘብ ለመስጠት የሚፈልጉ መሆኑን አስታወቁ:: ሳይሳካ ሲቀር ባመቱ ይህን ትልቅ ተቋም ከሁለት ከፈለ:: ከዚህ ወዲህ ቤተ ክርስቲያንን ሰላም ነሳ፤አንዱን ከአንዱ ጋር እንዲጋጩ አደረገ:: ያም ሆነ ይህ በወያኔው ቡድን ዓላማ በሚቀጥለው ግንቦት ይወገዛሉ ተብለው ስማቸው ከተያዘው አንዱ አዲስ ሐዋርያ አባ ወልደትንሣኤ አያልነህ ናቸው::

# ምዕራፍ 2

## አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ በተለያዩ ቦታዎች ተባረሩ!

ሶስና 1፤42 "በሐሰት እንደ ማሉኝ አንተ ታውቃለህ፤እነዚህ መምህራን ክፉ ነገርን ባደረጉብኝ ገንዘብ የሠራሁት ኃጢአት ሳይኖር እነሆ እሞታለሁ"የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በአባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ላይ ደርሷል። ዮሐንስ 12፤24"የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች" የሚለውን የወንጌል ቃል ይዘው ከአንዱ ሲባረሩ ከአንዱ ሕደው ወንጌል የሚዘሩ ናቸው። አባ ገብረ ሥላሴ በወያኔ መንጋ ከቦታ ቦታ ሲያባርሯቸው ከመርገም መመረቅን መርጠዋል። አሁንም እነዚህ ሰዎች እጀረጅም በመሆናቸው ይተኙላቸዋል ማለት አይቻልም። "ያዴቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም"እንደሚባለው ነው።

በተለይ አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡን ያሳደዱአቸው መጽሐፍት መጻፍ ከጀመሩ ወዲህ ነው። አብሶም ሕግ ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን? የሚለው መጽሐፋቸውን እንደጻፉ ወያኔ አስርጎ ያስገባቸው ሴረኞች ተነሱባቸው። ያም መጀመሪያ ኒዮርክ ሰላም እንዲባረሩ አደረጉ። ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ወደ ሲያትል እንዲመጡ አደረጉና "እነሆ አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ሲያትል መጥተዋል። ያስተምሯችኋል ይጠቅሟችኋል ተጠቀሙባቸው "ብለው ለምዕመኑ አስረከቡ። አባ ገብረ ሥላሴ ምዕመኑን ተግተው ማስተማር ጀመሩ። ሰኞ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፤እሮብ ከአዳራሹ፤ሀሙስና ቅዳሜ በቴሌ ኮንፍረንስ፤ እሁድ ከአውደ ምሕረቱ ወንጌልን መስበክ ጀመሩ። ይህ በዚህ እያለ አንድ ጠንቀኛ መጽሐፍ ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ ወጣ።

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ፤ይሕን መጽሐፍ አንብበው ዝም ማለት አልፈለጉም። ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳስ ጋር ሁነው መልስ አዘጋጁ። መጽሐፉ ተጽፎ አልቆ ለሕትመት ዲሲ ላኩት። ታዲያ ማተሚያ ቤት ያለው ግለሰብ መጽሐፉ እንዲታተም ባለመፈለጉ 7 ወር አስቀመጡት። እንዲያውም ለአዲስ አበባው ሲኖዶስ መድረሱ ተሰማ። ይህ የማተሚያ ቤት ያለው ግለሰብ አባ ገብረ ሥላሴ ስልክ ሲደውሉ የማያነሱ ሆኑ።የአዲስ አበባው ሲኖዶስ መጽሐፍ አንብቤው ስለነበር ከእነሱ ይልቅ እኔን ሰላም ነሳኝ። አባ ገብረ ሥላሴን "ፋይሉ



አለዎት ወይ"ስላቸው ሰጡኝ። እኔ መጽሐፍ ከማሳትምበት ወስጄ ከተስማማሁ በኋላ የሂሳብ ጉዳይ የሆነውን አባ መጥተው እንዲመለከቱ ሆነና ያ ለአዲስ አበባው ሲኖዶስ መልስ ተጻፈ።

የማይገለጥ የተከደነ የለም የሚል መጽሐፍ ታተመ። ይህ መጽሐፍ ከማተሚያ ቤት ወጥቶ ሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሲደርስ መምህር ሊቅ ዲ/ር አንዱዓለም ዳግማዊ ሲያዩት በጣም ተናደዱ። በወቅቱ የተመከኘው" ለሰላሙ እንቅፋት ይሆናል ብለው ነው"ተብሎ ነበር። ይህን መጽሐፍ ያዩት ቀን መምህር አንዱዓለም" አሞኛል"ብለው ሳያስተምሩ ቀሩ። እርሳቸው 2002 ዓም የሐምሌ ገብርኤል ጉባኤ ሲያትል ሊያስተምሩ መጥተው ነበር። ይህ በዚህ እንዳለ 2003 ዓም ዋሽንግተን ዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የተነሳው ችግር እንዲፈቱ አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ከብፁዕ አቡነ ያዕቆብና ከብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ጋር ሲኖዶስ ይልካቸዋል። እነዚህ አባቶች የተመለከቱትን ስህተት ዘርዝረው ገልጸዋል። በወቅቱ የደረሱበትን ተግባር ለመፈጸም እንቅፋት እንደገጠማቸው ሳይቀር ቃለ ጉባኤ አዘጋጅተዋል።

<u>በዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ</u> ገብርኤል ካቴድራል የተፈጠረውን ችግር አስመልክቶ ከጁን 28-2011 ጁላይ 11-2011 በቅዱስ ሲኖዶስ ልዑካን የተዘጋጀ ቃለ ጉባኤል"ይላል። ከዚህ ቃለ ጉባኤ "ከዚህ በፊት ተልኮ የነበረውን የቅዱስ ሲኖዶስ ልዑክ የወሰነው ውሳኔና መመሪያ መሠረት በማድረግ ተጀምሮ የነበረውን ሥራ እንዲፈጸምና በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ልዑካንን ላከ። ልዑኩም መገኘት አለበት በተባለበት ዕለት በዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ኃይል ካቴድራል ተገኘ። ልዑኩ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ከየት መጀመር እንዳለበት ውይይት ካደረገ በኋላ ከኛ በፊት መጥቶ የነበረው የቅዱስ ሲኖዶስ ልዑክ የወሰነውንና የሰጠውን መመሪያ መሠረት ያደረገ ትክክለኛ አጀንዳ አዘጋጀ"ይላል።

በግንቦቱ 2003 ዓም ሲኖዶሱ እነዚህን ሁለት ሊቃነ ጳጳሳትና አንድ መነኩሴ ከመላኩ በፊት ሌሎች አባቶች ችግሩን እንዲያዩ ልኮ ነበር። እነዚህም ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ፤ብፁዕ አቡነ ኤልያንሳ፤ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል፤ አባ ገብረ ሥላሴና ቄስ ገዝሃኝ፤ ቤተ ክርስቲያኑ በህግ ይተዳደር የሚል መመሪያ ሰጥቶ ነበር። ይህን አድርገው ከተመለሱ በኋላ ነው አባ ገብረ ሥላሴ ከሌሎች ጋር ሁነው የሄዱት።

በመጀመሪያ ሕደው ሳለ የተሰጠው መመሪያ ሳይፈጸም ስላገኙት ያነን በማስታወስ ጠንከር ያለ አቋም ይዘዋል።

በዚህ ወቅት የዲሲው ቡድን በአባ ገብረ ሥላሴ ላይ ማሴር ጀመረ። የዲሲው ተባባሪ የሆኑት የሲያትሉ አባ ታደሰ የኋላሸት፤ለአባ ይትባረክ ስልክ ደውለው "ገብረ ሥላሴ ሲያትል የተባረረ መሆኑን ንገረው"ብለው አዘዙ። አባ ይትባረክ "እኔ ተባረዋል ብዬ አልናገርም" ብለው እምቢ አሉ። ከዚያም አባ ታደሰ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ "ለአባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ስልክ ይደውሉና እንዳይመጡ ንገሩ" ብለው አዘዙአቸው። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ለአባ ገብረ ሥላሴ ስልክ ደውለው "ሲያትል እንደተባረሩ ንገሩ ተብለው የታዘዙ መሆናቸውን" አስረድተው ነገሩአቸው። በዚህ ሰዓት የሲያትል ምዕመን "ለምን ተባረሩ"ብሎ ጠየቀ።

<u>ብፁዕ አቡነ ሉቃስ</u> "እርፊህ ቀጭ በል ብለን ብንመክረው አልሰማም አለ። እናንተ ደሞዝ እየከፈላችሁት እርሱ እየዞረ አስቸግሮ ነው" አሉ። ለግማሹ ደጋፊያቸው ደግሞ "ይኸው ሳይነግረንና ሳያስጠነቀን ሔደ"ሲሉ ተናገሩ። አስቀድሞ ይህን እንዲናገሩ የተዘጋጁት አሽከሮቻቸው ከተማውን በወሬ ሞሉት። በብዛት ያስወሩት ዛሬ በአባ ታደሰ የቆብ ስም የተመሠረተው የማህበረ ሥላሴ ማኅበር አባላት ሲሆኑ አቶ ፀጋው ደምሴ፤ግንባር ቀደም ናቸው። ሌላው አባ ገብረ ሥላሴም የተጠሉበት ዘማሪ የዛሬው መላከ ጸሐፊ ቀሲስ እንዳልካቸው ከዲሲ ገብርኤል ታገዱ። ኋላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሲከፍቱ አባ ገብረ ሥላሴ ሕደው አበረታቱ። እንዲሁ ኦክላንድ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ተመላልሰዋል። በዚህ ምክንያት ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተዳምሮ ጠላት አብዝቶባቸዋል። አብሶም ለስለስ ባለ አንደበታቸው ለማስጠላት ጥረት ያደረጉት ብፁዕ አቡነ ሳውሮስ ግንባር ቀደም ናቸው።

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ <u>ሲኖዶሳዊው ጉዞ በኦርቶዶክሳዊ ቀኖና ሲመዘን</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 170 "ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ መሰናክል ገጥሞት ከሕዝብ እንዲለይ ይፈለጋል። ለዚህም ዓላማው ተፈጻሚነት በስደተኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም እንዳይኖር ይጥራል። ይህ ደግሞ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከተሰደደበት ዓላማ ጋር የሚፃረር ነው"ይሉና ገጽ 186 "ልዩነቱ ድጋፍ ሰጭዎች ለሚያደርጉት ስህተት በዕድሜ የሸመገሉ አባቶችን ድጋፍ የሚል



ቅባት ጨምረው መታየታቸው ነው"ይሉና ገጽ 204 "ሲኖዶስ ያወጣውን ደንብ አንጠቀምም በማለት የግለልተኛ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ሕግ ኮፒ አምጥተው የካቴድራል መተዳደሪያ ደንብ ያደረጉት በዚህ ምክንያት ይመስላል"ሲሉ ጽፈዋል።

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ጥቅስ ብዙ የወያኔን ወዶገባ ቡድን በማበሳጨቱ በአባ ገብረ ሥላሴ፤ ላይ ጥላቻን አሳድሮባቸዋ። ለዚህም ስብሰባ ላይ እንዲጠቁ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። በጥቅምት 2006 ዓም የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ ብፁዕ አቡነ መልከጸዲቅ "መጽሐፉ ይቃጠልኝ"በማለት ተናግረዋል። ለመሆኑ ብፁዕ አቡነ መልከጼዲቅ ማንን ለማስደሰት ነው? ወያኔን ወይስ ቤተ ክርስቲያንን? የእድሜ መግፋት ምልክት በመሆኑ እንጅ እንኳን ይቃጠል ሊሉ ቀርቶ ብፁዕ አቡነ መልከጸረዴቅ አባ ገብረ ሥላሴ የጻፉትን መጽሐፍ መግቢያ ጽፈው ነበር።

አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ <u>ሕግን ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን?</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 6" በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ የሆነው የክርስትና ሕግ በፈረሰበትና የሕግ መምህራብን ነን የሚሉ ብዙዎች ለሃይማኖት ሕግ በመቆም ፈንታ ለግል ጥቅም ሲሉ መስሎ አዳሪነታቸውን በአረጋገጡበት በአሁኑ ሰዓት አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ የሕግ መፍረስ ባመጣው ጣጣ ምክንያት በስደት ላይ ሁነው ሕግ ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን? የሚለውን ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀታቸው ይህ ድካማቸው የጸሐፊውን ማንነት ከማሳየቱም በላይ በውስጡ የተመዘገበው እውነት ቋሚ ምሥክር ሆኖ ለትውልድ ሲተላለፍ ይኖራል። በዚህ ዓለም ያለ የመንግሥትም ሆነ የሃይማኖት ድንጋጌ ሲፈርስ የሕግ የበላይነት ሲጣስ የእውነት መዝገብ በመሆን ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ማሰማት የሚገባት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ነገር ግን በጊዜያችን አመፁ፤አድማው፤ተንኮሉ የሚነግሠው በቤተ ክርስቲያን ነው። የሚያነሱትም የቤተ ክርስቲያን ርዕስ ነኝ የሚሉ ናቸው።"

"ሐሰት ሲውል ሲያድር፤ደግሞም ሲደጋገም እውነት ይመስላል፤ ሁሉም እንደ እውነት አድርጎ ይይዘዋል። በዚህ ጊዜ የእውነት ጠበቃ ያስፈልጋል፤እውነቱን በቃል ይናገራል፤በጹሑፍም ይገልጻል፤ እውነትን በቦታው ያስቀምጣል። አበ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ስለ ክርስትና ሕግ የሚያውቁትንና በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ተፈጽሞ ያዩትን በዝርዝር በመጽሐፋቸው እንዳስቀመጡት እውነት ከቦታው ለቀቀ የሚያሰኘውን ዓለም አቀፍ የክርስትና ሕግ ተጥሶ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በወያኔ ግፊት በኃይል ከመንበራቸው እንዲነሱና አባ ጳውሎስ በድፍረትና በማናለብኝነት በተቀደሰው መንበር ላይ እንዲቀመጡ መደረጉ ነው፤ሕግ ጥሶ ሕጋዊ መሆን ይቻላልን ያሰኘውም ይኸው ነው"ሲሉ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ጽፈው ነበር።

ይህን ብለው የጻፉ አባት ዛሬ የአባ ገብረ ሥላሴን መጽሐፍ እንዴት ይቃጠል ሊሉ ቻሉ? የወያኔ ሴረኞች እውነት ከጭንቅላታቸው የሌለ በጥቅም የሠከሩ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶሱን ለማፍረስ ሲሉ እኒህን አባት ከልጆቻቸው ጋር ሊያጋጩአቸው ተነሱ። አባ ገብረ ሥላሴ ወያኔ በአገርና በሕዝብ፤በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርገውን ጭፍጨፋ ከማጋለጥ አልተቆጠበም። በተለይ ከሁመራ እስከ ጋንቤላ 1600 ኪሎ መሬት ለሱዳን ሲሰጥ ትክክል አለመሆኑን ሲኖዶሱ አምኖበት አባ ገብረ ሥላሴን ከደንበር ኮሚቴው ጋር እንዲሰበስቡ ልኳቸው ነበር። ይህም ለወያኔ ታላቅ መቅሰፍት ነው። ዋልድባ ገዳምን ለማረስ ወያኔ ሲያቅድ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ትክክል አለመሆኑን አምኖበት ለተባበሩት መንግሥታት ሳይቀር ደብዳቤ አስገብቷል።

ይህ ስደተኛው ሲኖዶስ በዚህ ከቀጠለ ውሎ አድሮ ከሥነ መንግሥት ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አንድ ሁኖ እንዳይነሳ ለማድረግ ከፍተኛውን ጥረት አድርጓል። በዚህ ምክንያት በተለያዩ ቦታዎች በእርሳቸው ላይ ብዙ ችግር ሲደርስባቸው ኑሯል። የስም ማጥፋቱ ዘመቻ ተጧጡፏል። ይህን ያደረገው ደግሞ ወያኔ አስርጎ ያስገባቸው ስላሉ ነው። አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ወንጌል ሲሰብኩ እንኳን የሕዝብ መነዳት የአገር መከፋፈልን አንስተው ከመናገር አልተቆጠቡም። ወያኔ ከአዲስ አበባ የታወቁ ወይዛዝርትን ወደ አሜሪካ ሲልክ ከአንዳንድ አባቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት የሚያደርጉ አሉ። በሲያትል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እንዲያዘወትሩ የተመቡት ወይዘሮ ፀሐይ አለማየሁ ይባላሉ።

እርሳቸው እሁድ ቤተ ክርስቲያን በሚመጡበት ቀን አንዷ ወይዘሮ ሞረሽ ወደ አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ሕደው "አባ ወይዘሮ ጸሐይ ስላሉ ዛሬ ስለ ፖለቲካ እንዳያስተምሩ" ተብለውም ተመክረው ነበር። በዚህ



ቀን እንዲያውም አባ ኢትዮጵያ የባህር በር ያጣችው በወያኔ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘር እንዲከፋፈል የሆነው በወያኔ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ጊዜ የደረሰበትን ውርደት የመሰለ ውርደት ከዚህ በፊት ደርሶበት አያውቅም" ብለው ሰብከዋል። ለዚህ ነው አባ ገብረ ሥላሴ ከሲኖዶሱ ተወግዘው እንዲለዩ ለማድረግ የተጣረቅ ወያኔንለማገዝ ይረዳል ተብሎ በመታሰቡ ምክንያት ነው።

ዘንድሮ 2006 ዓም ጥምቀት አውስትራልያ ከብፁዕ አቡነ ዮሴፍና ከብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ጋር ሕደው ለሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለገዛው ቤት ማጠናከሪያ ከ$49 ሺህ በላይ ብር ያሰባሰቡ ናቸው። ታዲያ ይህን የመሰለ ሰባኪ ለማውገዝ ወያኔ ቢጠላ ትክክል ነው። ምክንያቱም ወያኔ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲጠነክር አይፈልግም ደግሜ ደጋግሜ የምለው ወያኔ ሰላም ያሳጣው ነገር ቢኖር በስደት አገር በጎሳ ስም የተደራጀ ድርጅት እንጂ በኢትዮጵያ ስም የተደራጀ ተቋም ማየት አይፈልግም። እንደ አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ዓይነት አስተማሪ በኢትዮጵያ ስም የተቋቋመ ተቋም እንጂ የጎሳ ተቋም ማየት አይፈልጉም። አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ የወያኔን መጥፎ ጠባይ በአውደ ምህረት የሚሰብኩ መጽሐፍ ጽፈው የሚያስነብቡ ናቸው።

መጽሐፈ ምሳሌ 5፤16 "እግዚአብሔር የሚጠላው ስድስት ነገሮች ናቸው። ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፋዋለች፤ትዕቢተኛ ዓይን፤ ሐሰተኛ ምላስ፤ንጹሑን ደም የምታፈስስ እጅ፤ክፉ አሳብን፤ የሚያቀርብ ልብ፤ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር፤በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር፤በወንድማማች መካከልም ጠብን የሚዘራ" የሚለውን መጥላት እንዳለብን ጠንክረው አስተምረዋል። እያስተማሩ ናቸው። ይህን ከዚህ በላይ የጠቀስኩትን ወያኔ የሚፈጽም በመሆኑ ሰላም ነሳው። የጻፉት መጻሕፍት እንዲቃጠልላቸው ሳይቀር ጠየቁ።

አዲስ ሐዋርያ አባ ወልደ ትንሣኤ አውስትራልያ መሄድ ባይችሉም አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ ከላይ ስማቸው ከተጠቀሰው ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ሁነው በቦታው ተገኝተው ምዕመኑን አጸናንተው ለሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለገዛው ቤት ማጠናከሪያ ገንዘብ አሰባሰቡ። ይህን የመሰለ ውድ እቃ አንዳንዶቹ "ቤት አልባ እንዲሆን ሳላደርግ አልተውም"ያሉት አልገባቸው ብሎ እንጂ አባ ገብረ ሥላሴ ጥበቡ የአባታቸውን ቤት የሚሰሩ ናቸው።

ግማሾቹ ደግሞ ካሉበት ቦታ ሆነው ብሶታቸውን ማሰማት ጀመሩ:: መጀመሪያ ከሁዋላ ስለነበርኩ የሆነውን ሁሉ በቪዲዮ እንጂ በቅርበት በአካል አልተመለከትኩም፤አልሰማሁም::"

"በሁዋላ እንደተረዳሁት ግን ቦርዱ ያባረረው ወይም ያገደው አንድ ጎበዝ ሰባኪና የሱን መባረር ተከትሎም ሌሎች ዲያቆናት ወጥተዋልና ይምጡ የሚል ስሞታ ነው"ይሉና ገጽ 2 "በሌላው አንጻር ግን በስብከቱ ወደር የሌለውን መምህር ለመፈንቀል ጥረት እየተደረገ ነው የሚል ክስ አለ:: ዶ/ር ነጋ ጉዳይ ሲያብራሩ ከምእመኑ ብዙ ክስ ቀርቦበት ሁለተኛም ማንም ዲያቆን ክህነት ከመቀበሉ በፊት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር ቦርድ መፍቀድና መወሰን አለበት፤ጳጳሱም ያንን ስርአት ሳይከተሉ ነው ሊያቀስሱት የጣሩት የሚል መልስ ሰጥተዋል"ሲሉ በዓይን ያዩትን ጽፈው በድረ ገጽ አስነብበውናል::

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ አይታወቅም:: ሰበካ ጉባኤ አንድን ሊቀ ጳጳስ ቅስና አትስጥ ማለት አይችልም:: እኔ ራሴን ለማቅለጳጳስ ሳይሆን በእናት ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ብዛት ያላቸው መጻሕፍት አንብቤአለሁ:: አንድም ሰበካ ጉባኤ መከልከል ይችላል የሚል መጻሕፍት አላነበብኩም:: ይህ ለወደፊቱም እንዳይደገም:: አንድ ሊቀ ጳጳስ ክህነት መስጠት ካልቻለ ታዲያ ከምኑ ላይ ነው ሊቀ ጳጳስነቱ? በዚህ በአሜሪካን አገር አብሶም በስደተኛው ሲኖዶስ ስር ያሉት ወያኔ የሚያዛቸው ሰበካ ጉባኤ፤በዚህ ከቀጠሉ ቄስ ሁነን ቤተ መቅደስ እንግባ እንዳይሉ ያሰጋል?

ሮሜ 16፤18"እንዲህ ያሉትን ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮልም የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ"የሚለው በዲሲው ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የዋሕ ምዕመናን አሳስተው አንድነትን ለማፍረስ ከጸረ የኢትዮጵያ ድርጅት ተልከው የመጡ ናቸው:: ስለዚህ ባለው ሠነድ መሠረት መላዕከ ጸሐይ በግንቦት 2006 ዓም እንዲወገዙ ስም ዝርዝር ከተያዘላቸው አንዱ እርሳቸው ናቸው::



# ምዕራፍ 4

## ሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ ባወቅ ሆኑ እንዲጠሉ

ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4፤10 "እኛ ስለ ክርስቶስ ሞኞች ነን፤እናንተ ግን በክርስቶስ ልባሞች ናችሁ፤እኛ ደካሞች ነን፤እናንተ ግን ኃይለኞች ናችሁ፤እናንተ የከበራችሁ ናችሁ፤እኛ ግን የተዋረድን ነን እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤እንጠማለን፤እንራቆታለን፤በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን ሲሰድቡን እንመርቃለን፤ሲያሳድዱን እንታገሳለን፤ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፤እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥርጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል"የሚለውን በተግባር የፈጸሙ የወንጌል ሰባኪ ናቸው::

ሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ፤አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ፤ዋሽንግተን ዲሲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በፖሊስ ተይዘው መሄዳቸውን በመቃወም ግንባር ቀደም ናቸው:: ከዚህ በፊት ተጽፎ እንዳነበብኩት እርሳቸው ኢትዮጵያ ሳሉ ከማህበረ ቅዱሳን ጋር አልግባባ በማለታቸው ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ለቀው ወደ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ገብተው ነበር:: ታዲያ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ንስሀ ሰጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልሰዋቸዋል::

ይህ በመሆኑ ዛሬ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ እንዲሳሳቱ የሚፈልገው ቡድን "ከጴንጤ ያወጡትን አባት አልታዘዝም አለ"እያሉ ያወራሉ:: ወደ ጴንጤ መሄዳቸው በንስሀ መመለሳቸው እርሳቸው አልካዱም:: ሊቀ ሕሩያ ቀሲስ መላኩ ማኅበረ ቅዱሳን ከቤተ ክርስቲያን እንዲወጡ ሲያደርጓቸው ተገደው ወደ ጴንጤ ሄዱ:: አዲስ አበባ ሳሉ ሲኖዶስ ይቅርታውን ተቀብሎ ንስሃ ሰጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዲመልሳቸው ደብዳቤ አስገብተው ለሁለት ዓመት መልስ አጥተው የቆዩ መሆናቸው ከዚያም አሜሪካ ሲመጡ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አቤቱታቸውን ተቀብሎ ንስሃ ሰጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው የመለሳቸው መሆኑን አልካዱም::

ቀሲስ መላኩ ባወቅ <u>ነጸብራቅ መጽሔት</u> ሚያዝያ 1995 ዓም ገጽ 14 "ራሴን ለአባቶቼ በማቅረብ ይቅርታ በመጠየቅ ከአባቶችና ከአንዳንድ ወንድሞቼ ጋር ከተነጋገርኩ በኋላ በ1992 ዓም ይፋ

ይቅርታ ደብዳቤ በአባ ጳውሎስ ለሚመራው አስተዳደር አቅርቤአለሁ። ነገር ግን ለሁለት ዓመት ጉዳዩን በመከታተል ብጉላላም ወደ ቤተክርስቲያኔ የሚመልሰኝ ይቅር የሚል አባት አጥቼ በጉዳዩ አዝኜ ሳለሁ በአጋጣሚ በአገኘሁት የጉብኝት እድል ወደ አሜሪካ በመምጣቴ በስደት ለሚገኘው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን በማቅረብ አባቶቼም ሁኔታውን መርምረው በይቅርታ በንስሐ ቀኖና ቤተክርስቲያን በሚፈቅደው ተቀብለውኛል" ሲሉ ጽፈዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማቴ 4፥17" መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ንስሐ ግቡ" ብሎ አይደለም እንዴ አስተማረ። ሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ በይፋ በጹሑፍ ይቅርታ ጠይቀው ንስሐ ተሰጥተዋል። የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ጸሐፊ መሆናቸውን ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ አልፈለጉም ለዚህም በ2006 ዓም ኮሎምበስ ኦኋዮ በነበረው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ እርሳቸውን አንስተው መምህር ሊቅ ዶ/ር አንዱዓለም ዳግማዊ ሹመዋል። ይህ አሰራር እንኳን በአንድ ክርስቲያን መሪ ቀርቶ ማንም ሰው ሊፈጽመው የማይገባ ነው ምክንያቱም ለመበቀል ታስቦ እንጂ ሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ ያለ ምንም ጥፋት ከጸሐፊነት ማንሳት ትክክል አይደለም።

የብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ መካሪዎች እርሳቸውን ለማሳሳት ሲሉ የሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩን ታሪክ እያነሱ ማስወራት ጀምረዋል። ታዲያ ሊቅ ዶ/ር ነጋ አለማየሁ፤ ይቅርታ የጠየቁበት ደብዳቤ መኖሩ አይታወቅም፤እርሳቸው "የበሃ" ሃይማኖት አማኝ ነበሩ። ይህን ታሪክ አንዴ ከቴሌ ኮንፍረስ ስብሰባ ላይ ሲነገር ሰምቻለሁ። እንዲሁም የደብረ ታቦር ልጆች ዋሽንግተን ዲሲ ቅዱስ ገብርኤል የሚሄዱ ነግረውኛል። ሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ አሜሪካ ብቻ ሳይሆን ካናዳና አውስትራልያ ብሎም አፍሪካ ተጉዘው በሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ስር ያሉትን ምዕመኑን የሚያጽናኑ ናቸው ለወደፊቱ ይህን አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱ ናቸው።

እርሳቸው ማስተማር ብቻ ሳይሆን ዘምረው ምዕመኑን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመልሱ ናቸው። አሁን ግን ይህን ተግባር እንዳይፈጽሙ ለማድረግ ታስቦ በሚመጣው ግንቦት 2006 ዓም የሲኖዶስ ስብሰባ እንዲወገዙ ስማቸው ከተያዙት መካከል አንዱ እርሳቸው ናቸው።



# ምዕራፍ 5

## መምህር ተከስተ ጫኔ ያላሉትን አሉ ተብለው ተከሰሱ!

ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ በላከው መልዕክቱ 3፥11"ጻድቅ የለም፤ አንድ ስንኳ አስተዋይም የለም እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፤በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ቸርነት የሚያደርግ የለም፤አንድ ስንኳ የለም። ጉሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው"ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ መልዕክቱ ጽፏል። ዛሬ መድረክ ማግኘትና የጠሉትን ማውገዝ የወደዱ ሁሉ ያልመሰላቸውን ሰው ሲጠሉት ይታያሉ።

በተለይ አንዳንድ መምህራን ዝም የሚሉ ከሆነ አፈ ሙሌዎች እንደ መብረቅ ድምጻቸው እየነጎደ የሚያሳስዱ ሁነዋል። የጳውሎስ መልዕክት ወደ ሮሜ 8፥7"ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና" ማን በገንዘብ እንደሚሰብክ አሳምረን እናውቃለን በየሄዱበት ቀን ስንት ዶላር እንደሚሰጣቸውና "ይህን ብለህ ስበክልን "ተብለው የተነገራቸውን የሚናገሩ መምህራን በበዙበት ዘመን እውነትን የያዙ ግን ወዳጅ በምድር ያነሳቸው መምህራን በዝተዋል። ከነዚህም መካከል አንዱ መምህር ተከስተ ጫኔ ናቸው።

መምህር ተከስተ ጫኔ ቀደም አክላንድ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበሩ። የቤተ ክርስቲያኑ ቦርድና አባ ቃለ ጽድቅ ሲጣሉ ወገናዊነት ሳያሳዩ ቆዩ። እንዲያውም "ከሁላችሁ አልሆንም" ብለው አክላንድን ትተው ዳላስ ሄዱ። እርሳቸው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን አስከፍተው የመጡ ናቸው ተብሎ በሌሎች ዘንድ ተወሰደ። አሁን እርሳቸው ዳላስ ቤተ ክርስቲያን አቋቁመው ወደ ቅዱስ ሲኖዶስ ለመግባት ጥረት ሲያደርጉ ከሳሻቸው ሊቅ ዶ/ር መምህር አንዱዓለም መሆናቸው ክርስቲያኑን ምዕመን ከልብ አሳዝኗል። መምህር ዓንዱዓለም እኖር የሊቀ ሕሩያን ቀሲስ መላኩ ስልጣን ስለተሰጣቸው ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ ናቸው።

የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ እንዳይፈቅዱ ብዙ ሲያጥሩ ከቆዩ በኋላ ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓም በግልጽ ከሲኖዶሱ ስብሰባ ላይ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መስጠት እንዳለበት ተናግረዋል። መምህሩ ግን እጅግ በጣም አድርገው ተቃውመዋል።

# ምዕራፍ 6

## አባ ቃለጽድ ሙሉጌታ መጋጨት የፈጠረው ችግር

ያዕቆብ 2፤14“ወንድሞቼ ሆይ!እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል?” የሚለውን ጥቅስ አንድ የአክላንድ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ምዕመን ለአባ ቃለጽድቅ ነው ሲሉ ነግረውኛል:: ሌላው የመድኃኒዓለም ምዕመን ደግሞ“ እውቀትና እምነት አይገኛድ አይደለም”ብለውኛል:: ይህ በአባ ቃለጽድቅ የግል ሕይወት ዙሪያ ያላቸውን ግምገማ ያቀረቡበት ጉዳይ ሲሆን አክላንድ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን ችግር የተፈጠረበትን ምክንያት በተቻለ መጠን ከሰዎች ጠይቄ ከተረዳሁት ሌላ ለዚህ ምዕራፍ የጠቀመኝ ነገር ቢኖር የኦዲት ዘገባው ደርሶኝ ካነበብኩ በኋላ ነው:: ብዙ ሰዎች ታሪኩን አዛብተው ነግረውናል:: እውነቱን ግን ያወጣው የቁጥጥር ኮሚቴው ወይም የኦዲት ሪፖርት ነው:: ይህን የኦዲት ሪፖርት የጻፉት ከዚህ በታች ስማቸውን የምጠቅሳቸው ሲሆኑ አቶና ወይዘሮ የሚለውን ማዕረግ ከመጣጥፉ ስላልተመዘገበ አልፌዋለሁ::

1ኛ መለሰ ከበደ፤2ኛ ዘነቡ በቀለ፤3ኛ አሸቱ ሽንቁጤ ናቸው:: ይህ ዘገባ የተጻፈው በጥቅምት 20 ቀን 2004 ዓም ነው:: የመጣጥፉ ርዕስ “ለመላከ ሰላም አባ ቃለጽድቅ፤የመካነ ሰላም መድኃኒዓለም ካቴድራል አስተዳደር ቦርድ ሊቀ መንበር ከኦዲትና ኢንሴፔሽን” ይላል:: ይህ መጣጥፍ የጠቡን መነሻ ዘርዝሮ ያቀርባል፤ ጌዜ ወስደው የሰሩት ለመሆኑ ጥርጥር የለኝም:: ከዚህ መጣጥፍ ጥቅስ ስወስድ “ከኦዲትና ኢንስፔክሽን”የሚለውን ጽፌ ጥቅስ እወስዳለሁ:: “ግልባጭ፤ 1ኛ ለብፁዕ አባታችን አቡነ መልከጼዴቅ፤ 2ኛ ለመካነ ሰላም መድኀኒዓለም ካቴድራል አስተዳደር ቦርድ፤3ኛ በዚህ ጉዳይ ላይ ለተመሰረተው አስታራቂ ኮሚቴ”ይላል::

<u>ከኦዲትና ኢንስፔክሽን</u> የተባለው የመጣጥፍ ርዕስ ገጽ 1“ጉዳዩ በመላከ ሰላም አባ ቃለ ጽድቅና በአቶ ቢንያም ሙሉጌታ መካከል ስለተፈጠረው አለመግባባት” ይልና “መላከ ሰላም አባ ቃለ ጽድቅ አባታችን አቡነ መልከጼዴቅ መኖሪያ ቤት---በስማቸው ስለተመዘገበ የባንክ ብድር አቶ ቢንያም ሙሉጌታ በደል አድርሶብኛል ብለው



በጻፉትና ባቀረቡት የሠነድ ማስረጃዎች እንዲሁም አቶ ቢንያም በሰጠው መልስና ባቀረበው ማስረጃዎች መሠረት ኦዲትና ኢንስፔክሽን ከምዕመናኑ በተሰጠው አጠቃላይ ኀላፊነት የተነሳ የዚህ የቤት ብድር እዳ የካቴድራሉ የንብረት እዳ በመሆኑ ስለ ጉዳዩ የቀረበለትን ሰነዶች በመመርመር የደረሰበትን ትንታኔና ውሳኔ ከዚህ ማስታዎሻ ጋራ አያይዞ ልኳል”ይላል:: ቤቱ ሊገዛ የቻለበትን ምክንያት ሲያብራራ እንዲህ ይገልጸዋል::

ገጽ 3 “ብፁዕ አባታችን ከካቴድራሉ በጣም ሩቅ ቦታ ስለሚኖሩ በቅርብ ሆነው ካቴድራሉን እንዲመሩ በአካባቢው ቤት በኪራይ ተፈልጎላቸው እንዲገቡ የአስተዳደር ቦርዱ ወሰነ:: የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ አሁን የሚኖሩበት ቤት ለሽያጭ ቀርቦ ስለነበረ ቤቱን ለመግዛት ተወሰነ:: ካቴድራሉ ከፍተኛ ብድር ስለነበረበት በባንክ የብድር መመዘኛ ሚዛን ሊደፋ ስላልቻለ ሌላ ተበዳሪ መፈለግ ግድ ሆነ:: የተጠየቁት የካቴድራሉ አባላት በሙሉ ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው አቶ ቢንያም መላከ ሰላም አባ ቃለጽድቅን አግባብቶ በእርሳቸው ስም ካቴድራሉ እንዲበደር ተደረገ”ይላል:: በዚህ መሠረት በአባ ቃለጽድቅ ስም 670 ሺህ ብር ቤት ይገዛል:: ይህ ከሆነ በኋላ እንግዲህ እዳው ሳይከፈል ቤቱ ወደ ካቴድራሉ ተዛውሯል:: ነገር ግን እዳው አሁንም በአባ ቃለጽድቅ ስም ነው:: ይህን ደግሞ የቁጥጥር ኮሚቴው ዘገባ እንዲህ ይገልጸዋል::

የኦዲትና ኢንስፔክሽን ገጽ 4“እ.አ.አ.በ07/106 የንብረቱ ግዢ ውል በተፈጸመበት ዕለት በመላከሰላም አባ ቃለጽድቅ ንብረቱን ወዲያውኑ ለመካነ ሰላም መድኀኒዓለም ካቴድራል ሲያስተላልፉ ዕዳው ደግሞ በዚያችው ዕለት ከመላከሰላም ወደ ካቴድራሉ መተላለፍ ነበረበት:: ይህ አልሆነም! የተገባላቸው ቃልም ተሠረዘ:: ይኸው እስካሁንም ድረስ ከዕዳ ባለመውጣታቸው አቤቱታቸው ሁሉ የመረረ ሆኖአል” ይላል:: በአቶ ቢንያም በኩል ደግሞ አባ ቃለጽድቅ በዋስ እንጂ በገዥነት አይደለም ብለው የተከራከሩ መሆናቸውን አስመልክቶ ገጽ 5“አቶ ቢንያም መላከሰላምን ዋስ እንጂ ገዢ አይደሉም ብሎ ያቀረበውን ማስረጃ ከላይ በተገለጸው ዝርዝር መሠረት አልተቀበልነውም”ይላል ዘገባው::

ገጽ8“መላከሰላም አባ ቃለጽድቅ የንብረት ጌዢ መሆናቸው እየታወቀ የገዥው ሠነዶች በሙሉ በእርሳቸው እጅና በካቴድራሉ ጽ/ቤት

በተለይ ቅዱስነታቸው ታመው ባለመገኘታቸው ወደገባው ቡድን ብፁዕ አቡነ መልኪጻዴቅን ይዞ የድል ቀኑን አክብሯል። ዳዊት ደጋሚዎችን በአባ ገብረ ሥላሴ ላይ እርግማናቸውን ሲያወርዱባቸው ሰንብተዋል። ይህን ዜና አባ ሰላማ ድረገጽ አውጥቶታል።

<u>አባ ሰላማ ድረገጽ ሰኞ</u> ሕዳር 2 ቀን 2006 ዓም ገጽ 2 "በመጨረሻም ሲኖዶሱ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍን ከምክትል ጸሐፊነት በማውረድ መላከ ገነት ገዝኸኝን በቦታው ተክቷል። በአትላንታ በተደረገው ስበር ስብሰባ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ይውረዱልኝ የሚል አቤቱታ ማቅረባቸውን እርሳቸውም ኃላፊነቱን እንደማይፈልጉ ይቅርብኝ ብለው እንደነበር ፓትርያርኩ ግን አይሆንም ሥራዎትን ዝም ብለው ይስሩ በማለት መወሰናቸውን ዘግበን ነበር። በዚህ ጉባኤ የፓትርያርኩን አለመኖር እንደ አጋጣሚ በመጠቀም የተጀመረው ሐሳብ ፍጻሜ አግኝቷል" ሲል ድረገጹ ዘግቧል። ምክትል ጸሐፊነቱ ሊሰጣቸው ታጭተው የነበሩት የሲያትሉ አባ ታደሰ ነበሩ። እርሳቸው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን አልታዘዝም በማለታቸው ወደ ቄስ ገዝኸኝ ስልጣኑ ተሻገረ።

ሊቀ ጳጳሱና አባ ታደሰ፤የተጋጩበት ምክንያት እንዲህ ነው። ብፁዕ አቡነ ሉቃስ ከአትላንታው ስብሰባ ሕደው ሳለ ሲያትል በመምህር ልዑለ ቃል አካሉ፤ ቤተ ክርስቲያን እንዲከፈት ተስማምተው ነበር። ከአትላንታ ከተመለሱ ወዲህ ጳጳሱ አቋማቸውን አባ ታደሰ አስቀይረዋል። በእውነቱ ከሆነ ሲያትል ቤተ ክርስቲያን እንዲከፈት ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ጥረዋል። በዚህ ተግባራቸው የክብረ ቅዱሳን ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ሊያመሰግኗቸው ይገባል። ክብረ ቅዱሳን መድኃኒዓለምን ምሥረታ ለማብሰር ቅድሚያ የወንጌል ጉባኤ ሲዘጋጅ ጀምሮ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በስልክ አባ ታደሰን አናግረው የተሰጣቸው መልስ ጥሩ ባለመሆኑ ምክንያት ተጋጩ። በዚህ ምክንያት ምክትል ጸሐፊነቱ ወደ ቄስ ገዝኸኝ ተሻግሯል። ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ አይጥሉ እንጂ ከጠሉ አይድረስ ነው። በተለይ አሁን እርጅናው ጓዙን ጠቅልሎ የገባባቸው በመሆኑ አልታዘዝ ያለውን ሲበቀሉት ይታያሉ።

<u>ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ</u> "የኔ ልጅ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በእድሚያቸው መግፋት ብዙ ነገሮች እየተበላሹብን ነው። እርሳቸው እድሚያቸው 110 ዓመታቸው ነው"ሲሉ ነግረውኛል። ታዲያ እኒህ



አረጋዊ አባት ቢሳሳቱ ተጠያቂ ማን ነው? እኔ እርሳቸውን ተጠያቂ ለማድረግ አልፈልግም። የብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅን እድሜ አስመልክቶ አንዱ ምሁር እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

<u>ሊቀ ዶ/ር ሞረሽ</u> "በ1964 ዓም እኔ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ስመለስ በተማሪዎች ማህበር ስብሰባ እካፈል ስለነበረ ደሕንነት ከኤርፖርት ሳልወጣ አሰረኝ። የማውቀው ሰው እኔ መታሰሬን ለዛሬው ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ስልክ ደውሎ ነገራቸው። እርሳቸውም ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ መታሰሬን ተናገሩ። ጸሐፊ ትእዛዝ ለደህንነት እንድፈታ አዘዙ። መኪና ተልኮልኝ ወደ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ቤት ሄድኩኝ። እርሳቸውን ስማቸውን እንጂ አይቻቸው አላውቅም። በዘህ ሰዓት እድሜያቸው 70 ዓመታቸው ነበር"ሲሉ ነግረውኛል። ስለዚህ በኒህ ሊቅ አባባል 112 ዓመታቸው ነው። እኒህን አዛውንት ይዞ ነው የደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ገለልተኛ አስብለው ነገር ግን ካህናቸውን ወደ ሲኖዶሱ ስብሰባ እየላኩ ቃለ ጉባኤውን አስወስደው ከቤተ ክርስቲያናቸው የሚያስነብቡት። የቤተ ክርስቲያናቸው መተዳደሪ ደንቡ ገለልተኛ መሆኑን ራሳቸው ተናግረዋል።

ነሐሴ 29 ቀን 2005 ዓም ሊቅ ዶ/ር ነጋ አለማየሁ "እኛ እንደ ቅድስት ማርያም ገለልተኛ ነን"ብለው ተናገሩ። ወያኔ ባልተጠበቀ መንገድ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍን ሊበቀላቸው ፈለገ። እርሳቸውን ወደ ካረቢያ የላከ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ ነበር። ከካረቢያን ወደ አሜሪካ መጥተው የሕጋዊው ሲኖዶስ አባል ከሆኑ ወዲህ ሊቀ ጳጳስ የሆኑ። በዚህ ምክንያት ወያኔ ሰዎች አስገብተው አቡነ መልከጼዴቅን አሳምነው አሁን ተበቀሉአቸው። ወያኔ የፈለገው ምክትል ጸሐፊ የሆኑት ተሯሩጠው የማይሰሩት ድምጸ መረዋው ቀሲስ ገዝሃኝ ሆኑ። ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በዚህ በጥምቀት ወራት ከአባ ገብረ ሥላሴና ከብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ጋር አውስትራልያ ሕደው ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ለገዛው ቤት ክፍያ የሚረዳ $49 ሺህ ዶላር ያሰባሰቡ አባት ናቸው። ወያኔ እንዲህ ዓይነት ታታሪ ጳጳስ አይፈልግምና እርሳቸው ከምክትል ጸሐፊነት ከወረዱ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ድክመት እንዲያሳይ ይሆናል። በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ስም ሰዎችን አስገብቶ ከያዙት ምክትል ጸሐፊነት እንዲወርዱ ማድረግ በግንቦቱ ስብሰባ ለማስወገዝ ብፁዕ አቡነ መልከጼዲቅን እየወተወተ ይገኛል።

# ምራፅፍ 3

## ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የገጠማቸው ፈተና

የዮሐንስ ራእይ 2፤10"እነሆ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኒኒ ሊያስገባችሁ አለው፤ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ"የሚለውን የዮሐንስን መልዕክት ሳነብ በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ላይ የደረሰ መስሎ ታይቶኛል፡፡ ልክ ነው ፈተና፤ፈተና ሁኖ እንደመጣባቸው ያረጋግጣል፡፡ ምክንያቱም ለሰሚው ግራ ነው፡፡ ጳጳሱ የመሠረቱትን ቤተ ክርስቲያን በዓለማዊ ፍርድ ቤት ከሰሱ የሚባለው ታሪክ ዛሬም ነገም ወደፊትም ተመዝግቦ የሚቆይ ነው፡፡ ግን ደግሞ አገናዛቢ የታሪክ ጸሐፊ ካል ለምን እንዴት በማን ቅስቀሳ ችግሩ ሊነሳ ቻለ ብሎ ማብራራቱ የታሪክ ባለሞያዎች ድርሻ ይሆናል፡፡ በውኑቱ አሜሪካ ውስጥ ያለውን የስደተኛውን ቤተ ክርስቲያን ሰላም ያሳጣ ችግር የተነሳው ዋሽንግተን ዲሲ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ከሚመሩት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ ይህን ጠንቅቆ ለትውልድ የሚተው ጸሐፊ አስፈላጊ ነው፡፡ እኔ ባለኝ አቅም ትንሽ ፍንጭ ልስጥ፡፡

1ኛ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስደተኛውን ሕዝብ ተቃዋሚ በአንድ አድርጎ የያዘ መሆኑን አገርንና ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠፋው የወያኔው ቡድን ከውስጡ ባስገባቸው አባላቱ ጠንቅቆ አውቋል፡፡

2ኛ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ አዲስ አኤጴስ ቆጰስ የሾመበት ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ወያኔ ያሰደዳቸው ቅዱስነታቸው የሚያርፉበት ከዚህ ደብረ ኃይል ቅዱስ ብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ይህን አንድነት ለማጥፋት ወያኔ ግለሰቦችን በደካማ ጎናቸው ገብቶ ይዟል፡፡ በእርግጥ በወቅቱ የነበሩት የቦርድ ሊቀ መንበር ቤተ ክርስቲያኑን ያሳደጉ ቢሆኑም ቅሉ ምዕመኑ የመምረጥ ሆነ የመመረጥ መብት አልነበረውም፡፡ አቶ መሀሪ በላይ ብዙ ዓመት በሊቀ መንበርነት መርተውታል፡፡ በዚህ ምክንያት ቅድሚያ የተወሰኑ ሰዎች" የመምረጥና የመመረጥ መብት ይኑር" የሚል ጥያቄ በግል ማንሳታቸው አልቀረም፡፡ ከዚህ ላይ ሊረሳ የማይገባው ነገር ቢኖር



እነዚህ ፍትህ ይኑር ያሉትን ግለሰቦች ጥያቄ የወያኔው ሰውር ቡድን ተጠቅሞበታል፡፡ በወቅቱ ያስወሩት "ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ደብረታቦሬዎችን አይወዱም" ብለው ሲሆን ሌላውን ጎንደሬ ሲያገኙ ደግሞ የሚሉት "አቶ መሀሪ በላይ ከደብረታቦር ውጭ ሌላ ሰው አይፈልግም"ብለው ነበር፡፡ አንዳንዱ ቅናቅን ወገኔ ሁኔታውን ረጋ ብሎ ከማጥናት ይልቅ ግንፍል ብሎ ቀጣውን የገለጠም ነበር፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ የተወሰኑ ግለሰቦች የቤተ ክርስቲያኑ አባላት ያልሆኑ ስም ዝርዝር አዘጋጅተው ለቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ አቀረቡ፡፡ 61 ሰዎች ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያኑ ችግር አለበት ብለው አቤት ብለዋል፡፡

በዋሽንግተን ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልና በአካባቢው የምንገኝ ለሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሰሜን አሜሪካ በተባለው ደብዳቤያቸው "እኛ በዋሽንግተን ዲሲ የደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራልና በአካባቢው የምንገኝ በስደት ላይ ያለውን ሕጋዊውን ቅዱስ ሲኖዶስ የምንከተል ምዕመናን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረ አንዳንድ አለመግባባቶች ቤተ ክርስቲያናችንን ሊጎዳ የሚልች አስተዳደራዊ መዋቅሩን ሊያዛባ የሚልች ነገር መስሎ ስለታየን ለቤተክርስቲያኑ የበላይ ኃላፊ ለሆነው ለቅዱስ ሲኖዶስ ይህን ማስታወሻ ለመጻፍ ተገደናል"ይልና፡፡

"ሆኖም ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተሠራው እንዳልተሠራና ይህንን ድካም ገደል የሚከት ከዚያም አልፎ የቅዱስ ሲኖዶስ ማዕከልነቱን የሚፈታተን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ሁኔታው ምዕመናን ሳያውቁት ለአደባባይ የወጣበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቤተ ክርስቲያኗን ከዚህ ባደረሱት መካከል ከፍተኛ አለመግባባትን አስከትሏል፡፡ አሁንም በክርስቶስ ክርስቲያን የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚያስተምረን አንድ ሆነን እያንዳንዳችን የአንድ ሰው የተለያዩ ብልቶች ሆነን መሥራት ሲገባን ይህን ለመተግበር አልቻልንም፡፡ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለም መልካም ሊሆን እንደማይችል እዚሁ መገመት ይቻላል፡፡"

"ቤተ ክርስቲያኑ ለሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ማዕከል ሆኖ የተለያዩ አገልግሎቶች የሚከናወኑበትና በስደት ላይ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ክርክስቲያኖች መጠጊያ ስትሆን በተቃራኒው የኢትዮጵያንና የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን መዳከም ለሚሹ የልብ ቁስል መሆኑ ይታወቃል፡፡ አሁን ያለው ሁኔታ እንዲሁ እንዲቀጥል ከተደረገ ግን

መሰሪዎች በውስጣችን ገብተው ቤተ ክርስቲያናችን የማፍረስና አባቶችም የደከሙበትን ሐዋርያዊ ተግባር ገደል የሚከት ይሆናል። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያኑ ተጠሪነቱ በስደት ላለው ቅዱስ ሲኖዶስ በመሆኑና በአጋጣሚም ይህ ስብሰባ ስለሚካሄድ ሁኔታው ያሳሰበን ምዕመናን ይህን ማስታወሻ ጽፈን አባቶች ተነጋግረውበት የሁኔታውን አሳሳቢነት ተረድተው ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ለመፈለግ አያግዳቸውም ብለን ይህን ማስታወሻ ጽፈናል። በመሆኑም በአስቸኳይ በቦታውም ተገኝተው ችግሩን መፍትሔ የሚሰጡ አባቶች በሲኖዶሱ በኩል ቢመደቡ መልካም ነው እንላለን። ቤተ ክርስቲያኑ በአባቶች ሥር ሆኖ ምዕመናን በባለቤትነታቸው እንዲረጋገጥ ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያኑ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚተዳደር እንደመሆኑ መጠን ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያኑን በሕጋዊ መንገድ የሚረከብበትን ሁኔታ እንዲያመቻች እናሳስባለን"ይላል። የ61 ሰዎች ስም ዝርዝር ሰፍሮበታል።

ከ61 መካከል ሁለቱን በስልክ አናግሬ ነበር። አንደኛው "እንኳን ስሜ መግባቱን ላውቅ ቀርቶ የቤተ ክርስቲያኑ አባል አይደለሁም" ብለውኛል። ሌላው ደግሞ "የቤተ ክርስቲያኑ አባል ብሆንም የዚህ ዓይነት ስብሰባ ሆነ ውይይት ሲደረግ አላውቅም" ብለውኛል። አንዳንዶቹ ይህ ደብዳቤ ለቤተ ክርስቲያኑ ብጥብጥ በር ከፋች ነው ይላሉ። ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ጥቅምት 24 ቀን 2003 ዓም መሆኑን ያመለክታል። ግንቦት 2003 ዓም የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ ነገሩ ገንትሮ በመቆየቱ ቅዱስ ሲኖዶስ ወኪሎች ይልካል። ወኪሎቹ ችግሩ ቤተ ክርስቲያኑ በቃለ አዋዲው የማይመራ መሆኑን ተረድተው ምክር ሰጥተዋል። በዚህ ምክንያት አቶ መሀሪ በላይ ማስጠንቀቂያ ጽፈው አካባቢውን እንዲለቁ አደረጉ። ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ለሰላም የመጡት ጳጳሳት መባረራቸውን አልደገፉም። በዚህ ሰዓት ከፍተኛ የሆነ ጥላጫ አወረዱባቸው። ይህ ሁኖ ሳለ በግድ ቤተ ክርስቲያኑ ምዕመኑ ምርጫ እንዲያደርግ ይደረጋል። የአቶ መሀሪ ከቤተ ክርስቲያኑ ሊቀመንበርነት መልቀቅ ቤተ ክርስቲያኑን ሰላም አልሰጠውም። እንዲያውም ይባስ ብሎ ጳጳሱ ቅስና እንዳይሰጡ የሚከለክል ቦርድ ተመርጧል። ፈተናው ከማንም ይልቅ የመጣባቸው ለብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ነው።

እኚህ ጳጳስ ቅድሚያ ቅስና እንዳይሰጡ መከልከላቸው ትክክል አለመሆኑን በግልጽ ተናግረዋል። ውሎ አድሮ ቀሲስ እንዳልካቸው



ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሲከፍቱ ፈቃድ መስጠታቸው ችግሩ እንዲገነትር ሁኖአል። ይህ በዚህ እንዳለ ሰበካ ጉባኤው "ካህናቱ የሚኖሩበትን ቤት ልናድሰው በመሆኑ ከተከራየንላችሁ ቤት ግቡ"ብሎ መናገሩን አንዳንድ ሰዎች አስረድተውኛል። ሌሎች ደግሞ "ሰበካ ጉባኤው ብፁዕ አቡነ ሳሙኤልን ሊያባርር በመፈለጉ ምክንያት እስቦ ያደረገው ሴራ ነው"ይላሉ። ይህ በዚህ እንዳለ ሊቀ ጳጳሱ ውለው ሲመጡ የሚኖሩበት ቤት ተቆልፎ በማግኘታቸው በየሰዓቱ የሚወስዱት መድኃኒት በመታሸጉ ምክንያት ለሕመም ይጋለጣሉና ሆስፒታል ይተኛሉ። ቤቱ ሲታሸግ ንብረት ሆነ መጻሕፍት ሊያገኙ አልቻሉም። በዚህ ምክንያት የመሰረቱትን ቤት ክርስቲያን ከሰዋል። ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ችግር እንዲነሳ የሚፈልጉ ወያኔዎች ናቸው። ዛሬ ወያኔዎቹ በከሳሽ በኩልም ሆነ በተከሳሽ በኩል ችግሩን የሚያባብሱ ናቸው። በዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥላቻ እንዲስፋፋ ከፍተኛውን ወሬ በከተማው አስፋፉት። ክሱን በሽምግልና ለማየት ተሞክሮአል። ሽምግልናው አገም ጠቀም ያለ ተከሳሹን የሚጠቅም ነው።

<u>ፓትርያርክ መርቆሬዎስ</u> የቅዱስ ገብርኤልን በዓል በዲሲ አከበሩ የሚለው ጹሑፍ ገጽ 1"የደብሩና ያካባቢው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤል ቅሬታቸውን ለጳጳሳቱ፤ለፓትርያርኩና ለምእመናኑ ተናገሩ እርሳቸው የሰበካው ሊቀ ጳጳስ ሆነው ሳለ ዲያቆኑን ሊያቀስሱ ሲል ከቦርዱ ተቃውሞ እንደገጠማቸው ሰባኪውም እንደታገደ እሳቸውም ማቀሰስ እንደማይችሉ መነገሩ እንዳሳዘናቸው ተናገሩ" ይሉና በወቅቱ ሊቀ ጳጳሱ ሊወይኑ ናቸው ተብሎ የተወራው ተክሌ የሰሙ መሆናቸውን እንዲህ ሲሉ "ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ሳሙኤል በውጭው ሲኖዶስና በፓትርያርኩ ጵጵስና ቢቀበሉም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአባ መላኩ ወይንም አቡነ ፋኑኤል ጋር መገናኘት እንደጀመሩና ወደ አገር ቤት የመግባት ዝንባሌ አላቸው የሚል ክስ"እንደተወራባቸው ጠቅሰው ጽፈዋል። በነገራችን ላይ የዲሲው ቡድን አደናጋሪ መሆኑን ልጥቀስላችሁ እወዳለሁ።

የአዲስ አበባው ሲኖዶስና ስደተኛው ሲኖዶስ ውይይት ሲጀምሩ" ስደተኛውን ሕዝብ ከደው አገር ቤት ሊገቡ ነው"ተብሎ የተወራው ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ውስጥ ያሉ ጥቂት ወደገባዎች ናቸው። ሌላው ደግሞ በጥቅምት 2006 ዓም የሲኖዶሱ ስብሰባ ጊዜ ብፁዕ አፍቅሮተ ሴት አቡነ ማትያስ ዘሕወሓት አሜሪካ መጥተው ነበር።

ኮሎምቦስ የሄዱት አቡነ ማትያስ የብፁዕ አቡነ መርቆርዮስን ወንድም ለሽምግልና ይዘውት መጥተዋል:: ከተኙበት ቤት ሊጠይቋቸው ይሄዳሉ ብለው አስወሩ:: ለዚህም ነው አደናጋሪዎች ናቸው የምለው ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል መሄድ ቢፈልጉ እስካሁን ይሄዱ ነበር ማንም አይዛቸውም የተወራው ሁሉ ውሸት ነበር:: ሊቅ ዶ/ር ነጋ የደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሊቀ መንበር ከሆኑ ወዲህ ሲኖዶሱ በሽምግልና እንዲያልቅ ሰዎች መድቧል:: ለነገሩ ሽማግሌዎች ፍሬቢስ ናቸው:: እንኳን ሊያስታርቁ ቀርቶ ሰዎች ሲያስታርቁ አይተው አያውቁም:: አንዳንዶች ራሳቸው በአመለካከታቸው አንዳይና ናቸው:: የጻፉት ደብዳቤ አሳዛኝ ነው:: ከአንድ ትልቅ ተቋም አስታራቂ ተብሎ የተሰየመ አካል የአንዱን ብቻ ይዞ ሌላውን ማጥቃት የለበትም:: ብፁዕ አቡነ ሳሙኤልን አስመልክቶ የሰጠው ብይን እንጅ የአስታራቂ ተግባር አይመስልም:: <u>መስከረም 10 ቀን 2006 ዓም ለብፁዕ አቡነ ሳሙኤል</u> ዋሽንግተን ዲሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ዋሽንግነት ዲሲ ይላል:: ሌላውን ትቸው ከዋናው ውሳኔው ላይ ልምጣ::

1ኛ ለብዙ ዘመናት ያገለገሉበትን ቤተ ክርስቲያን በዓለም ፍርድ ቤት መክሰስና ያገለገሉበትን ሕዝብ ማሳዘን አግባብ ባለመሆኑ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል በደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ላይ የመሠረቱትን ክስ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያቆሙ፤እንዲያነሱ፤ እንዲሰርዙ" ይላል:: ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔ ወይስ ሽምግልና? በጹሁፍ እንዲህ ተብሎ አይጻፍም:: በቃል ቁጭ ብሎ ሊነገር ይችል ይሆናል፡ ጹሁፍእኮ ታሪክ ሁኖ ይቀመጣል:: ለወደፊቱ ሽማግሌ የምትሆኑ ማንኛችሁም ቢሆን ከዚህ በላይ የተጻፈውን ዓይነት ፍርድ በጹሑፍ መስጠት ማሸማገል ሳይሆን ጠቡን ማገንተር ይሆናል:: ይህንማ የገብርኤልስ ሰበካ ጉባኤ የሚለው አይደለም እንዴ? ከምኑ ላይ ነው ሽምግልናው? ይህ ሽምግልና ሳይሆን እንዲያውም ማስፈራሪያ ይመልሰኛል:: "በደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ላይ የመሠረቱትን ክስ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያቆሙ፤እንዲያነሱ፤እንዲሰርዙ" ይህ ሽምግልና ነው? አይደለም ወገንተኝነት ነው::

2ኛ "ከዚህ ቀደም በደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ለብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ሲከፈል የነበረው አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈላቸውና ለወደፊቱም ክፍያው በቋሚነት እንዲቀጥል



እንዲደረግ"የሚለው ብዙም የሚተችበት አይደለም መልካም ይመስላል በጥንቃቄ ሳጠናው ደግሞ ደሞዜን ካገኘሁ ብለው እንዲተው ለማድረግ የታቀደም ይመስላል::

3ኛ "ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ቋሚ መኖሪያቸውን አሁን ባሉበት ቦታ ማለትም በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በማድረግ የዲሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንደመሆናቸው መጠን አሁን ያለው ችግር በሰላም ከተፈታ በኋላ በበዓላትና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ወደ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እየሔዱ አገልግሎት እንዲሰጡ"የሚለው አሁንም አግባብ አይደለም:: ምንም እንኳ በአሜሪካን አገር የሚመሰረተው ቤተ ክርስቲያን የሕዝብ መሆኑ ቢታወቅም ቅሉ ከባዶ አስነስተው ከዚህ ያደረሱት አባት "በበዓላትና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ" የሚባለው ሽምግልና ሳይሆን ቦታውን ለማስለቀቅ ስለታሰበ ነው:: ይህ ሽምግልና ሳይሆን በተራ ቁጥር ሁለት የገንዘብ ጉዳይ አሳይተው ለመዝጋት ታስቦ ነው::

4ኛ "የዲሲ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንም አቡነ ሳሙኤል የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መሆናቸውን አምኖ በመቀበል ለአንድ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሚገባውን ክብር በመስጠት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ እንዲያደርግ" ምንድናቸው አስፈላጊ የሆኑ የሆነው? ከልብ ሽምግልና ከሆነ ለምን አልተዘረዘረም? በምን ዓይነት መንገድ ነው ክብር የሚሰጣቸው? በእምነታችን መሠረት ጵጵስና በመንፈስ ቅዱስ ተቀብለዋል ብለን እናምናለን:: ታዲያ አንድ ጳጳስ ማቀሰስ ካልቻለ ይህን መብት የተነፈጉ ሊቀ ጳጳስ እንዴት ባለ መንገድ ነው ሊያከብሩአቸው የሚችለው?ቅስና እንዳይሰጡ የከለከለበትን እንኳን አንስቶ ትክክል አላደረገም ያላለ ሽማግሌ ሊሆን አይችልም::

5ኛ "በሁለቱም ወገኖች በኩል ለጠበቃ የወጣውን ገንዘብ በተመለከተ ዐቢይ የሰላምና ዕርቅ ጉባኤ በጋራ አዘጋጅቶ ሁኔታውን ለምዕመናን በማስረዳትና አስፈላጊውን እርዳታ እንዲሸፍን ማድረግ"ይላል:: አባ ሚካኤል ሊቀ ጳጳስ የእርቅና ሰላም ጉባኤ ሰብሳቢ ብሎ ፊርማ እንኳ የለውም:: የሚገርመው ነገር እነዚህ አባቶች የወጣውን ገንዘብ ምዕመኑ እንዲከፍል ብለው የወሰኑት ምዕመኑን ቁጭ በል ሲባል ቁጭ የሚል ሕድ ሲባል የሚሄድ እቃ ማድረጋቸው አሳዛኝ ነው::